



ትንሣኤ



ዋጋው፡ ሃምሳ ሣንቲም

ቁጥር ፲፩

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ፡፡

አዘጋጅ
**ንቅዓ ጥበብ ወንድም**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በሁለት ወራት አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ፡፡

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ደብዳቤዎች

መጋቢት 5 ቀን 1970 ዓ.ም.

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ድርጅቱ እያሳተመ የሚያወጣውን መጽሔት በየጊዜው እከታተላለሁ ። ሙከራው መልካም ነው ሆኖም መጽሔቱ በቤተ ክርስቲያን በኩል ብዙ ሥራዎች ሊሠሩ የሚችሉትን በይበልጥ ጠቀም አለበት እላለሁ። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያኒቱ እጅግ በጣም ብዙ ካህናት አሉት፣ በእርግጥ በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚፈለግባቸውን ሥራ ሲያሟሉ ይታያሉ ። ታዲያ የሚያገኙት አበል በጣም አነስተኛ ነው ኑሮን ሊቋቋሙት ስለአልቻሉ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እየተው ሲሄዱ ይታያሉ ።

በቤተ ክርስቲያን አካባቢም ብዙ ችግረኞች ምጽዋት ለማግኘት ይሰበሰባሉ። የሰበካ ጉባኤም አባላት የሰባካ ጉባኤን አላማ አጥብበው ስለሚመለከቱ ሰው ሲሞት በአጥቢያው በነፃ እንዲፈታ የቤተ ክርስቲያኑ አጥር አርጅቶአል እናድሰው ፣ እገሌ ትህትና አይታይበትም እናባረው በማለት ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በየሳምንቱ ተወያይተው ይለያያሉ ።

በእኔ ግምት ግን የሰበካ ጉባኤ አላማ ለችግረኞች መጠለያና ራሳቸውን ችለው ሌላውን እንዲረዱ ማድረግ ፣ ንዋየ ቅድሳትን መጠበቅ ፣ ካህናት ከቤተ ክርስቲያን ከተለመደው አገልግሎታቸው ሌላ ስለስብከት ሕጻናትን ስለማስተማር ዘዶ ስለጥቃቅን የጐጆ እንዱስትሪ ማስጠናትና በሥራ ማስተርጐም ካህናትም ሥራ ፈት መስለው በየቤተ ክርስቲያኑ ከመታየት ተቆጥበው ሕብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ማስጠናት ይመስለኛል ።

ይህን እንድጽፍ ያስገደደኝ በየካ ቅ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ብዙ የችግረኞች ልጆች ወላጆቻቸው ምጽዋት ሲለምኑ ሕጻናቱም የመለመኛ መሣሪያ ሆነዋቸው በማየቴ ባጠገቤ የነበሩትን ካህን ለምን እርስዎ ሰብስበው አያስተምሩአቸውም ብላቸው የሰጡኝ መልስ በመጀመሪያ በአጥቢያው ያለው ሰበካ ጉባኤ እኔን በዚህ ዓይነቱ ተግባር ቢያሰለጥነኝ ልሠለፍ እችላለሁ ከዚህ በፊት ግን የሰበካ ጉባኤ አባላት በሚገባ ማሰልጠን ያሻል አሉኝ አንተስ ምን ይመስልሃል ?

ዲያቆን ገብረ መስቀል ፀምሩ
ከየካ ቅ ሚካኤል አካባቢ

ዲያቆን ገ መስቀል ፀምሩ መልሱን ራስህ ስለመለስከው ሌላ ሃተታ የሚያስፈልግ አልነበረም ። ቢሆንም የቤተ ክርስቲያንን ችግር አንተ ስታውቅላት እኔም ዝም ብየ ላልፈው አልፈልግም ።

የዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን በሰበካ ጉባኤ እንድ ትራመድ መደረጉ መልካም ነው ። ታዲያ ተመራጮቹ እነማን ናቸው ? ተመራጮቹን አንተው እንዳልከው የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በአስፈላጊው ትምህርት አሰልጥነው የአሁኗን ቤተ ክርስቲያን ባቀረብከው አስተሳሰብ እንዲመሩ አት የእኛም ፍላጐት ነው ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አ.አ

14-7-70

የልዩ ልዩ ሃይማኖት ተወካዮች በብሔራዊ ሸንጐ ተሰብስበው ጊዜያዊ አስተዋጽኦ አድርገው ለእናት አገር መርዳታቸው የሚያስመሰግናቸው ነው ? ታዲያ እንደዚህ ያለው ስብሰባ ይቀጥላል ? ወይስ በዚህ የሚያከትም ነው ?

መምህር ስብሐት ለአብ መብራቱ
ከአዲስ አበባ

ይቀጥላል እናት ሀገር ከእኛ ብዙ የምትፈልገው ስላላት በዚህ አያከትምም የእናት አገር ጥሪውም በሰፊው የታሰበበት ስለሆነ ጅመር ነው እንጂ አሜን የተባለ አይደለም ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም

ቍጥር ፲፩

# ማ ው ጫ

## ኦ ር እ ስ ት

| ርእስ አንቀጽ | ገጽ |
|---|---|
| ሥራዩን ፈጸምኩ | ፪ |
| በጸሎተ ሐሙስ የተገኘው ለውጥ | ፫ |
| «ሳይሠሩ ደስታ ሳይጾሙ ፋሲካ» | ፭ |
| «በሀገር ሃይማኖት አይለያየንም» | ፯ |
| ሁሉም ድርሻውን ሲያበረክት | ፲ |
| መ/ቅዱስ ለሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት | ፲፯ |
| የሰባት ዓመት ተጋድሎ የሥራ ውጤት | ፲፰ |
| የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን | ፳ |
| ክርስቲያን ወይስ ቤተክርስቲያን ? | ፳፪ |
| ቤተክርስቲያናችን በ ለውጡ እንቅር ትራመድ | ፳፫ |
| የዓለም አብያተክርስቲያናት ዜና | ፳፬ |
| የእግዚአብሔር ሀላዌ | ፳፯ |
| የመ/ቅዱስ ማኅበር ዓምድ | ፳፰ |



www.ethiopianorthodox.org

( ር እ ሰ   አ ን ቀ ጽ )

# ሥ ራ ዬ ን   ፈ ጸ ም ኩ

እባቶች «መብልን እንጂ ሥራን ለነገ ማለት አይጠቅምም» እያሉ ይናገራሉ ። በእርግጥም ይህ አባ ባል ትክክለኛ ስለሆነ ሁላችን ልንመራበት ይገባል ። ለምን ? ቢባል የሥራ ውዝፍ ምንጊዜም ቢሆን ለባ ለቤቱ ችግር እንጂ ጥቅም ሊሰጥ ካለመቻሉም በላይ ፤ ለሀገርና ለወገንም ውድቀትን ሊያስከትል ይችላል ። ክርስቶስ «ለነገ አትበሉ ነገ ለራሱ ያስባል» በማለት አስተምሯል ። ይህንንም አባባል በሥራ አን ፃር ወስደን ስንተረጕመው ዛሬ ሊሠራ የሚገባው ለነገ ፤ የነገውን ደግሞ ለተነገ ወዲያ እያሉ በመቅጠር ምንም ቁም ነገር ሳይፈጽሙ ከዚህ ዓለም የሚወገዱትን የአንዳንድ ሰነፎችን የሕይወት ታሪክ ያሳስበናል ።

የሰው ልጅ ሊሠራው የሚገባውን ሥራ ሁሉ ዕቅድ አውጥቶ በዕቅዱ መሠረት እየተከታተለ በሥነ ሥርዓት ካልሠራ ነገ እሠራዋለሁ በማለት ብቻ ግዳጅ ሊፈጽም አይችልም ። ምክንያቱም ነገ ፤ ነገን እየወ ለደ ሲሔድ አሳብና ጭንቀትም ሳይቀርለት ሥራውም ሳይሠራ ለዕድሜ ቀጠሮ የለውምና በመካከሉ አንድ አጋጣሚ ነገር ሊመጣ ስለሚችል ነው ።

ሥራ በዛብኝ የሚል እንጂ ሥራዬን ጨረስኩ ብሎ በድፍረት የሚናገር ሰው እምብዛም ያለ አይመ ስልም ። ምክንያቱም የሰዎች ባሕርይ ስንፍና የተዋሐደው በመሆኑ ከመሥራት ይልቅ ተቀምጦ መብላትን ስለሚያዘወትር ነው ። ይህ ባይሆን ኖሮ ሰው ሠራሽ ችግር ሁሉ ፈጽሞ ከዓለም ላይ ይወገድ ነበር ። አን ዱም ሌላውን እየጨቆነ በመግዛት እርስ በእርሱ መደብ ፈጥሮ ሌላው የደከመበትን እሱ ተቀምጦ ለመ ብላትና የሌላው ሰው ጉልበት ጥገኛ ሆኖ ለመኖር አይፈቅድም ነበር ። ታዲያ የዓለም ሰዎች ጠባይና ሁኔታ እንዲህ ከሆነ ሥራዬንጨረስኩ ብሎ ለመናገር የሚደፍር ማነው ?

ለዚህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ለመስጠት የሚችል በማንኛውም የሥራ ዘርፍ ተመድቦ በመሥራት ጉል በቱን ሳይቆጥብ ምርትን ለማሳደግ በሚደረገው ብሔራዊ ትግል ተሳታፊ ሆኖ የሚሠለፍ ሰው ብቻ ነው ። ነገር ግን በሰዎች ዘንድ ምቀኝነትና ተንኮል ፉክክርና ስንፍናም ስላለ በዓለም ላይ የምናየው ሥራ ሁሉ ወደኋላ ሲጐተት መታየቱ ሊያስደንቀን አይችልም ። በተለይም በሥልጣኔ ወደኋላ በቀሩት አገሮች ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በዚህ ጉዳይ በቅድሚያ ቢያስቡበት መልካም ነው ።

እስከዛሬ ድረስ ባለው የዓለም ታሪክ ውስጥ ሊሠራው የሚገባውን ሥራ ሁሉ ከግቡ አድርሶ ያለፈ አንድ ሰው ብቻ ነው ። እሱም የዓለም መድኃኒት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ይህንንም «አባት ሆይ ! እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ» ሲል በተናገረው መለኮታዊ ቃሉ ከማረጋገጡም በላይ ፤ ሥራው ራሱ ምስክር ሆኖ ሲታይ ይኖራል ።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለቀላል ሥራ ሳይሆን እጅግ ከባድ የሆነውን ሥራ ለማከናወን ነበር ። ያም ከባድ ሥራ በኃጢአት ምክንያት የጠፋውን የሰው ልጅ ሕይወት በራሱ መሥዋዕትነት ማዳን ስለሆነ ፤ ለዚህ ከባድ ሥራ ዝግጁ ሆኖ ከመቅረብ በቀር ምንም አማራጭ ነገር ሊፈጥር አልፈቀደም ። ስለ ዚህ ፴ ዘመን ሙሉ በዚህ ዓለም ሲመላለስ ከቆየ በኋላ ጊዜው ሲደርስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ የማ ስተማር ሥራውን ቀጠለ ። በዚህም ጊዜ ውስጥ ጾመ ፤ ጸለየ ። በጾሙም ወራት በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ (ታላላቅ ፈተናዎች) ተፈትኖ ሰይጣንን ድል ነሣ ። ለምፃሞችን ከለምፃቸው አነፃቸው ። ድውያንን ፈወሰ ። ጐባጦችን አቀና ። በአጠቃላይ በሽተኞችን ከሕመማቸው ከማዳኑም በላይ ፤ ሙታንን አሥነሣ ። ሌላም ተአምራትን ሠራ ። በዚህም ሥራው ተከታዮችን አበረከተ ። ብዙዎችንም ካሳመነ በኋላ ለመጨረሻው መሥ ዋዕትነት ሲቀርብ «የሰጠኸኝን ሥራ ፈጸምኩ» በማለት ተናግሮ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ ። በዚህምጊዜ በመስቀል ላይ ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራን ተቀበለ ። ተገረፈ ። በጦር ተወጋ በአምስቱ ቅንዋት ተቸነከረ ። በመጨረሻም «ሁሉ ተፈጸመ» በማለት ያቺን መራራ የሞት ጽዋ ጨለጣት ። አስቀድሞ በነቢያት እንደተ ነገረ ፤ በእሱ ቁስል እኛ ተፈወስን ። የሱም ሞት ለእኛ ሕይወት ሆነ ።

ጌታ ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር ሁሉን እንደፈጸመ ሊቃውንትም መጻሕፍትም ይናገራሉ ። ይህ መሆኑ ከታመነ ዘንድ ፤ የሱ ተከታዮች ሁሉ ልንፈጽመው የሚገባን መልካም ሥራ እንዳለ በቅድሚያ ማስታወ ስና ለሥራም መዘጋጀት ያስፈልገናል ። ክርስቶስ ሊሠራው የሚገባውን ሁሉ እስከ ሞት ድረስ ለኛ ሲል እንደፈጸመ ፤ እኛም እሱ ያዘዘንን መፈጸም ይገባናልና ።



# በጸሎተ ሐሙስ የተገኘው ለውጥ

በዓለማችን ብዙ የጸሎት ዓይነቶችና ብዙ የጸሎት ቀኖች እንዳሉ ከታሪክ እንረዳለን ፤ በዘመነ ኦሪትም የተለያዩ የጸሎት ዕለቶችና የጸሎት ዓይነቶች ነበሩ ።

ከብዙዎች አንዱ የጸሎተ ሐሙስ ዋዜማ የነበረው የፋሲካው በዓል ቀን ነበረ ። በዚህ ዕለት የእግዚአብ ሔር ሰዎች በኅብረት እየተሰበሰቡ ከግብፅ ባርነት ስላወጣቸው ያመሰግኑት ወደ ፊትም ከተመሳሳይ ችግር እንዲ ጠብቃቸው ይጸልዩ ነበር ።

ለሥጋዊው ዓለም የተለያዩና የሚ ለዋወጡ ሥርዓቶች እንዳሉ ሁሉ በመንፈሳዊው በኩልም የተለያዩ የሥ ርዓት ዘመናት ነበሩ ። እነሱም የአ በው ፤ ሥርዓተ ዘመን ፤ የኦሪት ሥር ዓት ዘመን ፤ የመሳፍንት ሥርዓት ዘመን ፤ የነገሥታት ሥርዓተ ዘመን የነቢያት ዘመን ናቸው ።

እነዚህ አምስቱ ሥርዓት በተለያዩና በተከፋፈሉ ዘመናት አልፈዋል ። በነዚ ህም ባለፉት ሥርዓቶች ውስጥ ብዙ ዓበይት ቁም ነገሮች ይካሔዱ ነበር ። ከነዚህም ቁም ነገሮች አንዱ የፋሲካ ዝግጅት ነበር ።

ይህ ዝግጅት ለሐዲስ የለውጥ ሥር ዓት መንጠልጠያ እርካብ ሆኗል ። አንድ በጊዜው ለምልሞና አብቦይታይ የነበረ ዛፍ ጊዜው ሲአልፍበት ቅጠ ሉና አበባው ይረግፋል ። በዚህ አንፃር የዓለምም ሆነ የመንፈሳዊው ሥርዓት ጊዜው ሲአልፍበት በው ስጡ ተሸክሟቸው የነበሩት አሮጌ መመሪያዎች ሁሉ እየተራገፉ ይወ ድቁና ሌሎች ለአዲሱ ሥርዓትምቹ የሆኑ መመሪያዎች በቦታው ይተካሉ ።

ጸሎተ ሐሙስ ባለፈው ሥርዓት ውስጥ የነበረውን ሥርዓተ ፋሲካየሻ ረና ለሐዲሱ ሥርዓት ከፍተኛ ቦታ የሰጠ ታላቅ የለውጥ ቀን ነው ። ከ ዚህ ላይ በጥንቃቄና በማስተዋል ልን መለከተው የሚገባን ነገር አለ ። እሱም ፋሲካ ምን እንደሆነ ማወቅ ነው ። ፋሲካ የሚበላ ነገር ብቻ መስሎ ይታይ ይሆናል ። ግን የሚበላ ነገር ብቻ አይ ደለም ።

የፋሲካን ትክክለኛ ትርጉሙን ማወቅ የምንችለው በፈርዖንና በእሥ ራኤል መካከል ያለውን ታሪክ ስንመ ለከተው ነው ። ይህ ስም የፈርዖን መራ ራና ጽኑዕ አገዛዝ ከእሥራኤል ትከሻ ላይ ሊወርድ በተቃረበበት ወቅት ለተ ፈጸመው መንፈሳዊ ተአምር የተሰጠ የመጠሪያ ስም ነው ።

እሥራኤል ከግብፅ ሊወጡ አቅራ ቢያ ብዙ ምልክቶች በግብፃውያንላይ ታይተዋል ። ከምልክቶችም የመጨ ረሻው ምልክት በግብፃውያን ላይየታ ዘዘው ከፈርዖን ልጅ እስከ እንስሳ በኩር ድረስ እንዲሞት ከአምላክተወ ስኖ የተፈጸመው ነው ።

እንደውሳኔውም ከመፈጸሙ በፊት እሥራኤል ይህ ኃዘን ከቤታቸው እን ዳይገባ እንድ ሊአደርጉት የሚገባ ቸው የተለየ ምሥጢር ተነግሯቸው ነበር ። ይህም ምሥጢር እያንዳንዱ የእሥራኤል ቤተሰብ በየቤቱ አንዳ ንድ ጠቦት አርዶ የደጃፉን መድረክ መቃንና ጉበን በደሙ እንዲቀባ ነበር ዘፀ- ፲፪ ፤ ፳፯ ። እሥራኤል ትእዛዙን ተቀብለው የቤታቸውን ጉበን ከቀቡ በኋላ ይህ የታዘዘው ምልክት በግብፃ ውያን ቤት እየገባ የአምላክን ትእዛዝ ሊፈጽም ከእሥራኤል ቤት ግን ባንዱ ስንኳ ሳይገባ በበሩ ደም የተቀባውን ደጃፍ በማየት በጣሪያቸው ላይ እያን ዣበበ አለፋቸው ።

ይህ ድርጊት እሥራኤል በቋንቋ ቸው ፋሲካ ብለውታል ። ይህም ባላ ችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላች ኋል ፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከናንተአል ፋለሁ ። እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሠፍቱ ለጥፋት አይመጣባ ችሁም ዘፀ- ፲፪ ፥ ፲፫ እግዚአብሔር ከተናገረው ቃል የፋሲካን ትክ ክለኛ የትርጉም መንፈስ ስንመለከት ማለፍ ፤ መራመድ ፤ መሻገር እንደማ ለት ሆኖ እናገኘዋለን ።

የበጉ ደም ፋሲካቸው ሆኖ ከፈር ዖን እጅ አላቀቃቸው ። የጊዜው መቅ ሠፍት እንዲራመዳቸውና ፤ እንዲያል ፋቸው አደረገ ። ከግብፅ ወደከነዓን ለመግባት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኗ ዋል ። «ይህም የማለፉ መሥዋዕት» እየተባለ ዘፀ- ፲፪ ፤ ፳፯ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሻገረ መጥቶ ከክ ርስቶስ ዘመን ደርሷል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የፋሲካ በዓል እንደታላቅ ቁም ነገር በናፍቆት ይጠብቀው ስለነበረ «ከመ ከራዬ በፊት ከናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እመኝ ነበረ አለ» ሉቃስ ፳፪ ፤ ፲፭ ። ይህ ፈቃዱ በግብር የሚገለጽ በት ጊዜ ሲደርስ ለብዙኃኑ የኃጢአት ይቅርታ የተዘጋጀ የአዲሱ ሥርዓት ምልክት መሆኑን አስገንዝቦ ሁሉም በኅብረት እንዲሳተፉ ደቀ መዛሙር ቱን አዘዛቸው ። ማቴ- ፳፮ ፤ ፳፯ በዚ ህም ሥርዓተ ለውጥ ምክንያት ብዙ ዓበይት የጥንት መመሪያዎች ረግፈ ዋል ።

«ወንድ ባሪያና ሴት ባሪያ መግዛት ብትፈልጉ በዙሪያችሁ ካሉት አሕዛብ ሴትና ወንድ ባሪያዎችን ግዙ» ዘፀ- ፳፰ ፤ ፵፬ የሚለውን አሮጌውን ሕግ አስወግዶ «ማንም ከናንተ ታላቅ



www.ethiopianorthodox.org

ሲሆን የሚወድ የናንተ አገልጋይ ይሁን ፤ ፊተኛም ሊሆን ቢወድ የናንተ ባሪያ ይሁን» የሚለውን አዲስ ሕግ ተካ ማቴ- ፳ ፤ ፳፮ ።

ከዚህም ጋር ያረጀውንና ለራሱ መንግሥት የማይስማማውን ጉርብጥብጥ ሥርዓት አውጥቶ ሲመጣል ያቀደውን መለኮታዊ እቅድ ወደግቡ ለማድረስ ሲልና የተገዘርን መንፈስ ከሚከተሉት ክርስቲያኖች ጭንቅላትለማጠብና ለመደምሰስ ሊአገለግል እንጂ ሲአገለግሉት እንዳልመጣና ቢአስፈልግም ሕይወቱን ስለብዙዎች ቋሚና ዘላቂ ሕይወት ሲል እንደሚሠዋ ያቀደውን መንፈሳዊ ዓላማ በግልጽ አስረዳ ማቴ- ፳ ፤ ፳፰ ።

ፍጹም አምላክ ፤ ፍጹም ሰው ሲሆን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን አዋርዶ እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞት እንኳ ሳይቀር የታዘዘ ሆነ ፊል-፪፤ ፯- ፰ ሲል ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች እንደመሰከረ ሁሉ ፤ በዚህ ዕለት ባጭር ታጥቆ ፤ ራሱን ዝቅ አድርጎ የተከታዮቹን እግር አጥቦ በቃል የገለጸውንና ያስተማረውን በግብር ተረጐመው ዮሐ-፲፫፤፬-፲፭ የዛሬ ፲፱፻፴፯ ዓመት አካባቢ ይህ አስደናቂ ለውጥ ሲደረግ ለጊዜው የለውጡ መንፈስ ያልገባው ጴጥሮስ ክርስቶስ እራሱን ዝቅ አድርጎ እግር ማጠቡን በከፍተኛ መንፈስ ተቃውሞ ነበር ። ሆኖም እኔ ካላጠብኩህ ከኔ ጋር አንድነትና (ማኅበራዊ ሕይወት)የለህም አለው ።

ያዲሱ ሥርዓት ተቃዋሚው ጴጥሮስ የለውጡን መንፈስ ፈጽሞ ሲረዳው ይህ ከሆነ እግሬን ብቻ ሳይሆን ራሴንና እጄን ሁሉ እጠበኝ ሲል መላ ሰውነቱ በአዲሱ ሥርዓት እንዲታጠብለት ሁሉ እኩል የሆነበት ፤ ጌታ ራሱን ዝቅ ያደረገበት ሎሌራሱን ከፍ ያደረገበት የእኩልነት መንፈስ በጌታችንና በአምላካችን የታወጀባት የተቀደሰች ዕለት ናት ።

በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስንመረምረው ሌላ የረቀቀ ምሥጢር በውስጡ ተሰውሮበት እናገኛለን ። ሥነ ምሥጢሩ ከምርምር በላይ በመሆኑ ለታላቁ እሥራኤላዊ ሊቅ ለኒቆዲሞስም ከሚአውቀው በላይ ሆኖበት ያስቸገረውና በኋላም በክርስቶስ የተገለጸለት ምሥጢር ነው ዮሐ- ፫ ፤ ፪- ፲ ። ይህም ከውሃና ከመንፈስ መወለድ የሚለው ትእዛዝ ነው ።

በሰው ልጆች ሥነ ባሕርይ ምርምር ሲመዘን ማንም ሰው በሕይወቱ ሊፈጽመው ከባድና ጭንቅ የሚመስለውን አስጨናቂ ጉዳይ በሕይወቱ በመፈጸሙ ብዙ የሱ ተከታዮች ለሆኑትክርስቲያኖች ሁሉ ከፍተኛኩራትንናየምራል ድጋፍን ሰጥቷቸዋል ።

ይህም ከባድና አስጨናቂ ጉዳይ ቀደም ብሎ ከታላላቅ ነቢያት ተናጋሪዎች አንዱ ኢሳይያስ በሱ መሥዋዕትነትና በሱ ደም ተከታዮቹ ሁሉ ዘለዓለማዊ ፈውስ የሚያገኙ መሆናቸውን በትንቢቱ የጠቆመው ፍሬ ሐሳብነው ኗ- ፺- ፲፪ በመጨረሻም ይህንን ትንቢት በሥራ ላይ ካዋለው በኋላ እሮጌውንና ጊዜው የመሸበትን ሥርዓት በኮመጠጠ እርሾ መስሎ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይህንን እርሾ እንዲአስወግዱት በሰፊው ካስረዳ በኋላ «ፋሲካችን ክርስቶስ መሠዋቱን አበሰራቸው ። ፩ ቆሮ- ፭ ፤ ፮-፰

ፋሲካ ምን እንደሆነ በአሮጌውና ባለፈው ሥርዓት አንፃር በሰፊው ተመልከተነዋልና የክርስቶስ ፋሲካነት ግልጽ ስለሆነ ፤ የሚቀረንአይሆ ንም ባጭር ለማየት በክርስቶስ ፋሲካነት ከሥርዓተ ኦሪት ወደአዲሱ ሥርዓተ ወንጌል ተሻገርን ። በክርስቶስ ፋሲካነት ትምክህተኞችና ምፃተኞች የነበሩ የስዱቃውያን ፤ የፈሪሳውያንና የጸሐፍት ትዕቢት ተናደ ። ተንቀውና ተጠቅተው ይኖሩ የነበሩ አሕዛብና ድሆች ልዕልናን ተጐናጸፉ ። ባንዳንድ ነቢያትም ከዕለታት አንድ ቀን እሕዛብ ከደስታቸው የተነሣ የፊነዳና የፊካ ጽጌ ረዳ ሲይዙ፤ አይሁድ ደግሞ ከትቢታቸውና ከኃጢአታቸው የተነሣ ለእግረ ሥጋና ለእግረ ሕሊና አስጨናቂ የሆነ እሾህና አሜከላ እንደሚ

ተከታዩ ወደ ፲፪ ኛው ገጽ ዞሯል




ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የመስነባበቻ ቅዱስ ራት እንደመገባቸው



# « ሳይሠሩ ደስታ ሳይጾሙ ፋሲካ »

የመልካም ሥራ ውጤቱ ደስታ ፣ ሲሆን ፤ የመጾምም መፈጸሚያው ፋሲካ ነው ፤ ሠርቶ በሥራው የማይደሰት ሠራተኛ ጹሞ በመጨረሻ የማይፈስክ ጾመኛ አይገኝም ።

በዚህ ዓለም ላይ ለተወሰነ ጊዜ እንዲኖሩ የተፈጠሩ ሰዎች ሁሉ እንደመልካቸው የተለየ ባህል ፤ የተለየ ቋንቋ የተለየ እምነት አላቸው ፤ በባህላቸው በቋንቋቸውና በእምነታቸውም መሠረት የሚፈጽሟቸው ልዩ ልዩ ተግባሮች አሏቸው ።



ፋሲካችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳለ ፡

ክርስቲያኖች ይጾማሉ ፤ ይሰግዳሉ ሌላም ብዙ መንፈሳውያን የሆኑ ነገሮችን በየጊዜው ያከናውናሉ ፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች ያልሆኑትም ሕዝቦች ቢሆኑ ከዚያው በሚያምኑት አቅጣጫ የሚያከናውኑት ሥራ አላቸው ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ወገኖች ለመደሰትና ለመኖር የሚችሉት በሚሠሩት የሥራ ውጤት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም ።

በዓለም ላይ ከሚኖሩት ሕዝቦች መካከል አንዳንዶች በኃይል በርትተው ዓለምን በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ አድርገው እንደያዙ የሚፈሩት ለሥራ ሳይለግሙ ለዕውቀት ሳይሠንፉ ሌት ከቀን በመሥራታቸው ነው ። ለሥራ ያልሠነፉ ሕዝቦች ራሳቸው ሠርተው ባገኙት የሥራ ውጤት በአየርይበራሉ በምድር ይሽከረከራሉ ፤ በባሕር ላይ ይንሳፈፋሉ ፤ ከዚህም አልፈው ተርፈው በሕዋው ላይ መንሸርሸር ከጨረቃ አካል ላይ ማረፍ ጀምረዋል ። በዚህም ሥራቸው የሚደሰቱትና የተደሰቱት ጠቢባኑ ብቻ አይደሉም ፤ ሥራቸው የሰው ልጅለሆነ ሁሉ የሚያስደስት የሚያስመካና የሚያኮራ ዓቢይ ኃይል ነው። ጠንክሮ መሥራት መፈላሰፍና መራቀቅ ኃጢአት አይደለም ። እግዚአብሔርም ፍልስፍናን አይቃወምም ጠንክሮ ሠርቶ የሥራን ውጤት ለተተኪው ትውልድ ማትረፍ የሚያስደስተው ሠሪውን ብቻ አይደለም ፤ በጊዜው ያለውንና ወደፊትም የሚተካውን



www.ethiopianorthodox.org

ትውልድ እጅግ በጣም ያስደስተዋል። ያኮራዋል ፤ ያስመካዋል ።

በአሁኑ ክፍለ ዘመን ዓለሙ ሁሉ በጠቅላላ ለሥራ ተሠልፎ ሌት ከቀን ይደክማል ፤ ይጥራል ፤ ይግራል ፤ይወጣል ይወርዳል ፤ ይህንንም የሚያደርገው አንዱ የሌላውን ሥራ ብቻእሻግሮ እየተመለከተ በማድነቅ ኑሮውን ለመገንባት ሳይሆን ፤በራሱ የሥራ ውጤት ለመደሰት ነው ።

እግዚአብሔር አምላካችን ለመጀመሪያው ሰው የሥራን ክቡርነት ሲያመለክተው ፤ « ብላዕ በሐፈ ገጽከ » በግንባርህ ወዝ ብላ ብሎታል ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጆች ከሥራ የተገለሉበት ጊዜ የላቸውም ፤ ሠርተው በሥራቸው ውጤት ራሳቸው ተደስተው ሌላውንም ያስደስታሉ ፤ ሐዋርያው ጳውሎስም « ሊሠራ የማይወድ ሰው አይመገብ » በማለት ተናግሯል። ራሳቸው ሳይሠሩ ሌላው የሠራውን ለመንጠቅ የሚቀመጡ ሌቦችና ቀማኞች የመሳሰሉትም ሁሉ ሠርተው መብላትን ይማሩ ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ መልእክቷን ከማስተላለፍ አትቆጠብም ።

አሁን በዓለም ላይ አምረው ሠምረው ፤ ደምቀውና አሸብርቀው የሚታዩት ነገሮች ሁሉ እምኃብ አልቦ ያለ ሥራ የተገኙ ሳይሆኑ ፤ የሰውልጅ የሥራ ውጤቶች ናቸው ። በኅብረተ ሰብአዊነት ፍልስፍና ለመራመድ መንገድን በመቀየስ ላይ የምትገኘው ሀገራችን ኢትዮጵያም ደስታ የሚወለደው ከሥራ መሆኑን በመረዳት ወንድ ሴት ትልቅ ሳይለይ ሁሉምእንደዕውቀቱና እንደችሎታው በሚያውቀውየሥራ መሥመር ተሠልፎ እንዲሠራ አድርጋለች ። ሁሉም በርትቶ ከሠራ ሀገራችን ሌሎች አህጉር ከደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ እንደምትደርስ እንተማመናለን ።

ይሁን እንጂ ብዙዎች በሥራቸው ውጤት ለመደሰት የሚችሉበትን ጊዜ በመናፈቅ ጠንክረው ሲሠሩ ፤ አንዳንዶች ሌላው በደከመበት ለመደሰት ሲጥሩ መታየታቸው እጅ በጣም የሚያሳዝን ነው ።

ወደመንፈሳዊ ክፍል መለስ ብለን ስንመለከት ደግሞ የክርስትናን እምነትን ለዓለም ለማዳረስ በርትተው የሠሩ ሐዋርያትና መሰሎቻቸው ሁሉ በሥራቸው መደሰታቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን ።

ሐዋርያትና ሰብአ አርዕድት ቅዱሳት እንስትም የተመረጡት በሥራቸው ነው በተመረጡበትም ሥራ ተሠልፈው ሲሠሩ እጅግ በጣም ይደሰቱ ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን ሰብአ አርድዕት የስብከት ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሳሉ ፤ የእግዚአብሔርን ስም ሲጠሩባቸው አጋንንት ከበሽተኞች ላይ እየለቀቁ በመውጣታቸው በጣም ተደሰቱ ፤ ከደስታቸውም ብዛት የተነሣ ወደ ክርስቶስ መጥተው ጌታሆይ ስምህን ብንጠራባቸው አጋንንት ከሰዎች ላይ እየወጡ ሄዱ ። በስምህ አጋንንት ተገዝተውልናል አሉት ፤ ክርስቶስም መልሶ መናፍስት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ በመንግሥተ ሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ » ብሏቸዋል ።

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ከሁሉም በይበልጥ ያስደስታል የፈጣሪውን ትእዛዝ ከዕለት ተግባሩ ጋርአጣምሮ የሚሠራ ሰው ደስታው በዚህ ዓለም ብቻ ተወስኖ አይቀርም ። ስሙ በመንግሥተ ሰማያት ስለሚመዘገብ ደስታው በዚህም በዚያም ዓለም የሠፈነ ዘለዓለማዊ ይሆናል ( ሉቃ-፲ ፡ ፲፯)

ሰብአ አርድዕት በሥራቸው አጋንንትን ከሰው ላይ አባረው በተደሰቱ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስምመደሰቱን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል ።ቅን መልእክተኛ ራሱ ብቻ ተደስቶ አይቀርም ፤ ላኪንም ያስደስታል ፤ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የሚደሰቱት ለምጽ በማንፃታቸው ፤ ድውይ በመፈወሳቸው ፤ አጋንንትን ከሰዎችበማስወጣታቸው ብቻ አልነበረም ታሥረው ሲፈቱ ተደብድበው ሲለቀቁ ፤ ይደሰቱ ነበር ። « ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፏቸው ፤ በኢየሱስ ስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘውፈቷቸው ፤ እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ ። ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ የማስተማርና የመስበክ ሥራቸውን አይተውም ነበር » ይላል ። እንግዲህ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ በኩል ደስታ ያለ ሥራ አለመገኘቱ ከታወቀ ወንዱም ሴቱም ካህኑም ትንሹም ትልቁምማንኛውም ሰው ደስታን ለማግኘት ጠንክሮ የመሥራት ግዴታ አለበት ።

« ሳይጾሙ ፋሲካ » የሚለውም ቃል ከዚሁ ጋር ይነፃፀራል ። በመንፈሳዊ አቅጣጫ በኩል አተኩረን ስንመለከት የነፍስ ደስታ የሚገኙባቸው በርከት ያሉ የሥነ ምግባራት ዘርፎችን እናገኛለን ፤ ከብዙዎችም የነፍስ ምግባራት አንደኛው ጾም ነው ። የጾም ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ሊገቱ የሚገባቸው ብዙ ፈቃዳተ ሥጋ አሉ ።

በጾም ወራት አጥንትንና ሥጋን ከሚያለመልሙ ፈቃደ ሥጋን ለተንኮል ከሚያነሣሡ ትዕግሥትን ከሚያሳጡ ምግቦችና መጠጦች መከልከል ያስፈልጋል ፤ ይህ ብቻ አይደለም ፤ በአፍ ክፉ ነገርን ከመናገር በጆሮ ክፉ ነገርን ከማዳመጥና እነዚህንና እነዚህን ከመሳሰሉትም ሥራዎች ተከልክሎ ጾም መፈሰክ እውነተኛ ዋጋን ያስገኛል ። ከተጠቀሱት ነገሮች ሳይከለከል ፋሲካ የሚያደርግ ሰው ግን ፋሲካን የሚያደርገው እንዲሁ በልማድ ስለሆነ ደስታው ፍጹምነት አይኖረውም ።

ሳይጾሙ ለመፈሰክ ፤ ሳይሠሩ ለመደሰት የሚመኙ ሰነፎች ሰዎች ሁሉ ዓላማቸው ትክክል ስላይደለ ወደፊት ጾመው ለመፈሰክ ፤ ሠርተው ለመደሰት እንዲችሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ መልእክቷን ከማስተላለፍ ወደኋላ አትልም ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ



# በሀገር ፤ ሃይማኖት አይለያየንም

በኢትዮጵያ ያሉ የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች «በሀገር ሃይማኖት አይለያየንም» በሚል ዓላማ ተነሥተው የሦስት ቀን ሴሚናር በማድረግ ስለእናት ሀገር ጥሪ ተወያይተው መግለጫ አውጥተዋል ።

መጋቢት ፲፱ ቀን ፸፭ ዓ/ ም/ በማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ውስጥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ጸሎተ ቡራኬ የተጀመረውን ይህን ሰሚናር በንግግር የከፈቱት ጓድ ሻለቃ እንዳለ ተሰማ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቋሚ ኮሚቴ አባልና የደርጉ የማኅበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ሲሆኑ ፤ የኦርቶዶክስ ፤ የካቶሊክ ፤ የፕሮቴስታንትና የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች ፤ እንዲሁም ከአንድ ሽህ ሁለት መቶ በላይ የሆኑ የነዚህ እምነት ተከታዮች የሰሚናሩ ተካፋዮች በመሆን በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ። በዚሁም ወቅት ጓድ ዶክተር ዓለሙ አበበ የአ/ አ/ ማዘጋጃ ቤት ከንቲባና ጓድ ሻለቃ ግርማ ንዋይ የአብዮታዊት ኢት/ ማዕከላዊ ዜና አገልግሎት ማሠራጫ ኃላፊ ተገኝተዋል ።

ጓድ ሻለቃ እንዳለ በሀገራችን ላይ ስለደረሰው ጊዜያዊ ችግርና ጠላቶቻችን በናት አገራችን ላይ ስለሚፈጽሙት ደባና ይህም አብዮት በአካሔዱ አገሮች ሁሉ የታየ ስለሆነ ያልተጠበቀ ጉዳይ አለመሆኑን ጠቅሰው ፤ በሃይማኖት ምክንያት ሊከፋፍሉን የሚፈልጉት ሁሉ የዚህ ጉባኤ ውጤት ሊያሳፍራቸው እንደሚችል በመግለጥ ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል ።

ጓድ ሻለቃ እንዳለ በዚሁ ንግግራቸው «የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮታዊ ትግል በዓለም ጭቁን ሕዝቦች ላይ የሚደረገውን ምዝበራን ፤ ጭቆናን ወረራን ፤ እንዲሁም የሃይማኖትና የጾታ አድልዎን በጥብቅ የሚቃወም የዓለም ጭቁን ሕዝቦች አካል በመሆኑ ሃይማኖትን የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው አብዮቱን ለመቀልበስና የሀገሪቱን ምድር ቆርሶ ለመውሰድ የሚሯሯጡትን ሁሉ እያጋለጣቸው ወደፊት ይገሰግሳል » ሲሉ ገልጠዋል ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ የተቀዳጃቸው ድሎች ከፍተኛ መሆናቸውንና ያሉትም ችግሮች በዚያው መጠን ከባድና መራራ መሆናቸውን ጓድ ሻለቃ እንዳለ ጠቅሰው ፤ በኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት የሚደራጁና የሚታዘዙ አድኃሪ መንግሥታት በአብዮታችንና በእናት ሀገራችንላይ የተነሡ በመሆናቸው የሞቃዲሾን የገዢ መደብ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ በማስነሣታቸው በአውሮፕላን ፤ በመድፍ ፤ በታንክና በልዩ ልዩ ከባድ መሣሪያዎች በመረዳት ግልጥ ወረራ አካሒደዋል ። ጉዳት ቢያደርሱብንም ፤ «እምቢ ለሀገሬ ፤ እምቢ ለነፃነቴ » ብሎ የተነሣውቆራጡና አብዮታዊው ሠራዊታችን ባደረገው ተጋድሎ የጠላትን ኃይል እየሰባበረና እየደመሰሰ ለጊዜውየተያዙትን ከተሞችና ሥፍራዎች ሁሉ ነፃ በማድረግ ለበለጠ ወሳኝ ፍልሚያ ትግሉን የቀጠለ መሆኑን አስገንዝበዋል ።

ጓድ ሻለቃ እንዳለ ተሰማ ንግግራቸውን በመቀጠል ፤ «ትግላችን መራራና ረጅም መሆኑን በማስገንዘብ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከታዮች ለሀገራችሁ ስትሉ በየቀበሌያችሁ ፤ በየመሥሪያ ቤታችሁና በየግላችሁ ከምታደርጉት የእናት ሀገር መዋጮ ሌላ ስለእናት አገር ጉዳይ ለመነጋገር በአንድነት በመሰብሰባችሁ የሃይማኖት ጦርነት በማወጅ የገንዘብና የጦር መሣሪያ በገፍ በማቀበል ላይ ለሚገኙት አድኃሪ የዓረብ የገዢ መደቦችና የሞቃዲሾ ዕብሪተኛ መንግሥት እንዲሁም «ኤርትራ ዓረብ ናት»ለሚሉም ተገንጣይ ቡድኖች ሃይማኖት የፖለቲካ መሣሪያ አለመሆኑን እንዲገነዘቡትና ከቅሌታቸውም እንዲማሩ አርአያነታችሁ ከፍተኛ ምሳሌ እንደሚሆን አያጠራጥርም » ብለዋል ።

በመጨረሻም ይህን ሰፋ ያለ ንግግራቸውን ሲደመድሙ የሰሚናሩተካፋዮች ውይይት የተሳካና ለኢትዮጵያ አብዮት ና አንድነት አስተዋጽኦ እንዲኖረው በመመኘት «ሃይማኖት አይለያየንም ድል ያለመራራ ትግል አይገኝም » ብለው ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክም በዚሁ በናት አገር ጥሪ ሴሚናር ላይ የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች በአንድነት በመሰብሰባቸው የተሰማቸውን ደስታና የሃይማኖት ተከታዮችም ስለሰላምና ስለ ትክክለኛ ፍትሕ በግልጥ እንደሚያስተምሩ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

## የቅዱስነታቸው ንግግር

« የተወደዳችሁ ወንድሞቼና እኅቶቼ ፤ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች »

በዛሬው ዕለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንስም



www.ethiopianorthodox.org

ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ስም ይህን የሦስት ዕለታት የእናት አገር ጥሪ ሴሚናር በቡራኬ ስከፍት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ስብሰባውን በቡራኬ ሲከፍቱ

ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማኛል ። ደስታዬ በክርስቲያኖቹ መሰብሰብ ብቻ አይደለም ። ወንድሞቻችን የእስልምና እምነት ተከታዮችም በአንዲት እናት አገር ማኅጸን አብረው የተወለዱ እንደመሆናቸው መጠን ፣ በዛሬው ዕለት ለዚህ ታላቅ ቁም ነገር አብረን በአንድነት መሰብሰባችን የጠቅላላ ክርስቲያኖችን ደስታ እጥፍ ድርብ አድርጎታል ።

ክርስቲያኖችም ሆኑ ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ስለሰላምና ትክክለኛ ፍትሕ እንሰብካለን ፣ እናስተምራለን ። ምንጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጐረቤት አገሮች ጋር በሰላም መኖርን ይወዳል ፣ የማንንም ምድር አይፈልግም ። የራሱንም በታላቅ ተጋድሎ ይጠብቃል ።

የሶማሊያ ገገርዎች የኢትዮጵያን ጀግኖች በፊት ለፊት ተዋግተው ሳይሆን በስውር ምስጢር ድንበር ጥሰው በመግባት አያሌ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችንና የእስላምና እምነት ተከታዮችን ጭምር በጭካኔ ፈጅተዋል ። በሀብታችን ላይም ከባድ ጉዳት አድርሰዋል ። አብያተ ክርስቲያናትንና መስጊዶችን አቃጥለዋል ። ይህ የሚገልጠው የሶማሌ ገገርዎች ለማንኛውም ሃይማኖት ያልቆሙ መሆኑን ነው ። የኢትዮጵያ ጀግኖች ትዕግሥተኞችና ሰላም ወዳዶች ቢሆኑም ፣ በግፍ ለመጣ የማያስ ይንበረከኩ ፣ ድንበራቸውን የማያስነኩ ለመሆኑ ሕያው የሆነው የአድዋ ታሪክ ምስክር ነው ። በማይጨው ጦርነትም ጠላት አሸንፎ ገባ የተባለው ከተማ ከተማውን ነበር እንጂ ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ በየሸለቆውና በየሸንተረሩ ከመውለብለብ አልተገታም ። ከአምስት ዓመታት በኋላም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላትን ደምስሶ ድልን ተጐናጽፏል ።

በአድዋም ሆነ በማይጨው ጦርነት ክርስቲያኖችም ሆኑ የእስልምና እምነት ተከታዮች በአንድነት ተካፋዮች እንደነበሩ ታሪክ ምስክርነው ዛሬም ለተመሳሳይ ችግር መፍትሔ ለማስገኘት በእናት አገር ጥሪ ምክንያት መሰብሰባችን የአንዲት እናት ልጆች መሆናችንን የምናስመሰክርበት በሃይማኖት ፣ በነገድ ፣ በዘር ፣ በቋንቋ ሊለያዩን የሚመኙትንና በተግባርም ለመግለጥ የሞከሩትን የሚያሳፍር ፣ የወደፊት አንድነታችንን የሚያጠነክር ነው ። ሃይማኖትናሥርዓት የየግላችን ሆኖ ሁላችንም የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ነን እንጂ ማንኛችንም ዲቃሎች አይደለንም ።

ከአሁንም ጀምሮ ለወደፊቱ ምንም ልዩነት ሳይኖርብን በእኩልነትና በነፃነት እንደየእምነታችን ክርስቲያኖች በየአብያተ ክርስቲያኖቻችን፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች በየመስጊዶቻቸው ለፈጣሪያቸው የሚገባውን ምስጋና እናቀርባለን ። ምሕረቱን ፣ ቸርነቱን ፣ ታዳጊነቱን እንለምናለን ።

ለሰው ልጆች እኩልነት ፣ ትክክለኛ ፍትሕ ፣ ነፃነትና ሰላም ሁላችንም በኅብረት መታገል ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው ። በአገራችን ከለውጡ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ኅብረተ ሰብአዊነት በሚያሻጋግር ጉዞ ላይ ይገኛል ። ይህ ጉዞው ለእኩልነት ፣ ትክክለኛ ፍትሕ ፣ ነፃነትና ሰላም መሆኑ ግልጥ ነው ።

በሃይማኖት ስም የግል ጥቅማቸውን ከሚያሳድዱ ጥቂቶች ግለ ሰቦች በስተቀር ፣ ማንኛውም ሃይማኖት በእኩልነት ፣ በትክክለኛ ፍትሕ ፣ ነፃነትና ሰላም ያምናል ፣ ያስተምራልም ። በተለይም በክርስትና እምነት የተገለጠ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተተነበየ ቃል እነሆ ፣ «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሠሩት መፈታትን ፣ ለዕውሮችም ማየትን ፣ እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል » ሉቃስ ፬ ፡ ፲፰—፳፩ ። በዚህ አንጻር ሁላችሁም የሰሚናሩ ተካፋዮች ከልዩ ልዩ ምሁራን ትምህርታውያን ንግግሮችን ካዳመጣችሁ በኋላ ከልብ ተወያይታችሁ ሰላምን ፣ ነፃነትን ፣ እውነትን ለሚወዱ ለኢትዮጵያና የዓለም ሕ ዝ ቦ ች ጠቃሚ የሆነ ፍሬ እንደምታፈሩ በሃይማኖት ስም የሚያወናብዱትን እንደምታሳፍሩ እናምናለን ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለቀደሙ አበው በታሪክ አንጻር በመንፈሳዊ መልእክቱ ሲመሰክር ፣ «እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ ፣ ጽድቅን አደረጉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ ፣ የአንበሶችን አፍ ዘጉ ፣ የእሳትን ኃይል አጠፉ ፣ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ፣ ከድካማቸው በረቱ ፣ በጦርነቱ ኃይለኞች ሆኑ ። የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ» ዕብራውያን ፲፩ ፡ ፴፪ —፴፬ ብሏል ።

የሶማሊያ ገገርዎች ከሕግ ውጭ ምድራችንን ቆርሰው ለመውሰድ ወታደሮቻቸው ስለእውነት ካልቆሙ የባዕድ ጭፍሮች ጋር በመሰለፍ ቢረባረቡብንም በሰሜን ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ችግር ቢገጥመንም መደበኛው መለዮ ለባሽና ሕዝባዊ ሠራዊት ጠንክሮ በመዋጋት የባዕድ ጭፍሮችንም ጭምር ተቋቁሞ የኦጋዴንን አውራጃ ነፃ በማውጣቱ በሐዋርያው መልእክት አንፃር ደስታው የሁላችንምነው ይህም የድሉ መጨረሻ ስላይደለ እስከ መጨረሻው ታግሎ በርቱ እንላለን ።

ሁላችንም የሃይማኖት ተከታዮችና ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሶማሊያ ገገር መደቦች የተቀደሰ ጦርነት በማለት በሃይማኖት ስም ተጠግተን ማንንም ማታለል አንፈቅድም ። ጀግኖቻችን የሚታገሉት ለድንበራቸውና ለእናት አገራቸው ክብር ስለሆነ የተቀደሰውና እውነተኛው የጀግኖቻችን ትግል መሆኑን ለጠላቶቻችንና እውነትን ለመረዳት ለሚፈልግ የዓለም ሕዝብ ሁሉ እናረጋግጣለን» በማለት እግዚአብሔር ስብሰባውን እንደሚባርከና የኢትዮጵያንም ሕዝብ በሰላም እንደሚጠብቅ ያላቸውን ምኞት በልባዊ ጸሎት ገልጸው ንግግራቸውን ደምድመዋል ።

ሐጂ መሐመድ ሳኒ የታላቁ መስጊድ ኢማምም ቀደም ሲል ባሰሙት ንግግር «ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀድሞዎቹ የገገር መደቦች ጨቁነው ለመግዛት እንዲያመቻቸው በሃይማኖትና በጐሣ እየለያዩና እርስ በርሱም እያጋጩ ሲያዳክሙት ቢኖሩም የውጭ ጠላት አገራችንን ለመውረር በተነሣ ጊዜ ሁሉ የተባበረ ክንዱን በማንሣት እያሳፈረ መመለሱን ጠቅሰው ፣ ማንኛውም ሃይማኖት በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የሚያስተምር ሲሆን፣ጥቂቶቹ ግን ሃይማኖትን የፍላጎታቸው ማርኪያ ፣ የግዛት ማስፋፋት ምኞታቸውን ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሲያደርጉት ኖረዋል ። ይሁን እንጂ ወረራ ፣ ብዝበዛና ጭቆና እስካሉ ድረስ ሰላም ከቶ ሊሠፍን እንደማይችል በሰፊው ገልጠዋል ።

እናት አገራችን በተቀነባበረ ሤራ ዙሪያውን በጠላት ተከባ ባለችበት በአሁኑ ወቅት ፣ ግልጥ ወረራም ተፈጽሞባት ድንበሯ ተደፍሮ ሳለ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚኖርበት የማንኛውም ሃይማኖት ተከታይ በየበኩላችን አድኃሪው ሥርዓት ያቆየንን ያለመተዋወቅ መጋረጃ በማስወገድ በቅን ልቡና ስለጋራ ሀገራችን ከመወያየት የበለጠ ቁም ነገር የለም ።ይህም ኅብረት በችግር ጊዜ ብቻ ሳይሆንበልማትም ሆነ በማንኛውም የሀገርጉዳይ ወደፊት መቀጠል አለበት» ሲሉ ሐጂ መሐመድ ሳኒ አስገንዝበዋል ።

በመጀመሪያም ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለሴሚናሩ ዓላማ ሲገልጡ ባደረጉት ንግግር «አድኃሪው የሞቃዲሾ መንግሥትና መሰሎቹ የአብዮታዊት እናት አገራችንን ህልውና ለማናጋት የተደጋገመ ሙከራ ቢያደርጉም ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ይልቅ አንድነታቸውን አጠንክረው በመቋቋማቸውና ጠላታቸውንም በማንበርከካቸው ወደፊትም ፋታ እንደማይሰጡት ጠላት ከመገንዘቡም በላይ ከዘር ሲያያዝ የመጣውን ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል» ብለዋል ። ቀጥለውም «እኛ ኢትዮጵያውያን የተለያየ ሃይማኖት ብንከተልም ከአንዲት ምድር ፣ ከአንዲት እናት ሀገር የተገኘን እንደመሆናችን መጠን ፣ በየጊዜው እየተገናኘን በመወያየት የጠላትን ሤራ ማክሸፍ አለብን» ብለዋል።

በዚሁ ከመጋቢት ፲፱ እስከ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም በአዲስ አበ ማዘጋጃ ቤትና በብሔራዊ ሸንጎ ሲካሔድ በቆየው የሦስት ቀን ሴሚናር ከተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ማለት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣ ከካቶሊክ ፣ ከመካነ ኢየሱስ ፣ ከመሠረተ ክርስቶስ ፣ ከሕይወት ብርሃን ፣ ከቃለ ሕይወት ፣ ከሉተራን ፣ ከሙሉ ወንጌል ፣ ከሠፈረ ገነት ፣ ከብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን ፣ ከአማኑኤል ባፕቲስትና ከክርስቶስ እምነት አብያተ ክርስቲያናት ፣ እንዲሁም ከእስልምና እምነት ተከታዮች በርከት ያሉ ልዑካን ተካፋይ ሆነው የዚሁ ሴሚናር አስተባባሪ ኮሚቴ ባወጣው ፕሮግራም በመጠቀም በርከት ባሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ውሳኔ አሳልፈዋል ።

በዚሁ ሴሚናር ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣት መዘምራን ፣ እንዲሁም የመሠረተ ክርስቶስና የሙሉ ወንጌል መዘምራን ፣ የእስልምናም ወጣት መዘም

ተከታዩ ወደ፲፫ኛው ገጽ ዞሯል






www.ethiopianorthodox.org

# ሁሉም ድርሻውን ሲያበረክት

«በሰላም እንድንኖር ያደረገን የሕዝባችን ትብብርና አንድነት ነው » ሲሉ አንድ ታላቅ መሪ ተናግረው ነበር ። በዚሁ አንፃር እኛም አሁን የሚያስፈልገን ይህ መሆኑን ተረድተን ስለምሥራቅ ጦር ግንባር ጉዳት ማድረስ ከአካባቢው የነበሩትን መምሬ ተዘራ ወርቁን ጠይቀናል ።

መምሬ ተዘራ ወርቁ የሐረርጌ ሀ/ ስብከት ሥራ አስኪያጅ እንደመሆንዎ መጠን ለመጠየቅ የፈለግሁት



በምሥራቃዊውና ደቡባዊ ክፍል ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች

እምባ ገነኑ የሶማሌ ገገር የሀገራችንን ዳር ድንበር ጥሶ ገብቶ በሐረርና በዙሪያዋ ባሉት ምዕመናንና ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱ ታውቋል ።

ስለዚህም መንግሥት በበኩሉ እነዚህን ሕዝቦች በማቋቋም ላይ ነው ያለው በእናንተስ በኩል እነዚህን ሕዝቦች አሁን ቀደም የረዳችሁት እንዳለ ቢገልጹልኝ ? ለወደፊትም ለመርዳት ዕቅድ እንዳላችሁ ቢያብራሩልኝ ?

<u>መልስ</u> ፣ አድኃሪው የሶማሌው መንግሥት መጀመሪያም ሲነሣ በሃይማኖት ፣ በጐሣ ከፋፍሎ የተነሣ ስለሆነ ፣ በምዕመናን ላይ ብዙ ችግር አድርሷል ። በይበልጥ በክርስቲያን በኩል ያሉትን እየመረጠ ብዙ የፊጀ መሆኑ ግልጽ ነው ። በዚሁ ምክንያት ተባረው በየሥፍራው ለመጡት መንግሥት በየመጠለያው ሲያስቀምጥ ፣ቤተ ክህነትም በበኩሉ በገንዘብ ረገድ ወደ አሥር ሺህ ብር ረድቷል ። ይኸውም ከልማት ኮሚሽን አምስት ሺህ ብር ፣ ከቁልቢ ገብርኤል አምስት ሺህ ብር በማዋጣት ረድተናል ። እንደዚሁም ደግሞ በቤተክርስቲያን ደረጃ ትምህርት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ሰባክያን ሁለተኛ ደግሞ ከየጦር ኃይሎች የነበሩትን አስተማሪዎች በየሥፍራው የነበሩትን ካህናት በማስተባበር እንዲያስተምሩ አድርገን ብዙዎች መጽሐፈ ቁደር እንዲጠመቁ የጠየቁ ስለነበሩ እነርሱ መጽሐፈ ቁደር እንዲጠመቁ አድርገናል ። ደግሞም ለሦስት ጊዜ ያህል ጸሎተ ፍትሐት በማኅበር እንዲደረግ ተወስኖ በጦርነትም ሆነ በድንገት ለሞቱት ምዕመናን ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል ። ወደፊትም ቢሆን ገንዘብ ከልማት ኮሚሽን ተጠይቋል ። በመጀመሪያ ምዕመናኑ የሚቋቋምበት ሁኔታ ነው ። ከዚያም ቀጥሎ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቋቋሙ ጥረት ይደረጋል ። በይበልጥ ምዕመናኑን መርዳት ስለሆነ ፣ በከፍተኛ ደረጃ በቅዱስ ፓትርያርኩ የበላይ ጠባቂነት ፣ በቅዱስ ሲኖዶስተወስኖ ወደ ፲፫ አባላት ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ገንዘቡን በመሰብሰብ ላይ ይገኛል ።

አሁን ደግሞ ከቁልቢ ገብርኤል ገንዘብ ላይ ለጊዜው አምሳ ሺህብር ለመጠገኛ ተብሎ የተፈቀደ አለ ። ይኸውም በዚህ ሰሞን ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ወደዚያው ተልኳል ። ልብሰ ተክህናም አሁን ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን የአምስት ልውካን ልብሰ ተክህኖ ፣ አንድ ሺህ ብር ፣ ሌላም ርዳታ ሁሉ በመጻሕፍትም በኩል በዘቢብም በኩል ርዳታ ተሰጥቶ ይህም በመላክ ላይ ይገኛል ። ለሕዝቡም ደግሞ ልማት ኮሚሽን ወደፊት እጥንትን ከውጪ አገር ጠይቀን እንረዳለን ብሏል ። ይህን በማድረግ ላይ ነው ያለነው ። ግን ሕዝቡ ከአሁን በፊት አብያተ ክርስቲያናትን የሚያስተዳድረው ሕዝቡ ነበር ፣ አሁንም ቤተ ክርስቲያኑን መልሰን ካቋቋምንለት ከፍተኛውን ወጪ እንደቻ



ልንለት ስለሚቆጥረው በመንግሥትም ደረጃ አንዱን ክፍል ቻልን ማለት ነው ። ምክንያቱም የነበረው እንዲጠፋ አይፈልግምና ነው ። ሕዝቡንም በመርዳት ፣ ቤተ ክርስቲያንም በማቋቋም ረዳን ማለት ነው ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ አሁን ቀደም የሠራችሁትንና ለወደፊትም ሊሠራ የታቀደውን በጥሩ ሁኔታ አብራርተውልናል ። ሥራውም የሚያስመሰግን ነው በዚያ ክፍለ ሀገር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደተቃጠሉ ሰምተናል ። ለመሆኑ ስንት አብያተ ክርስቲያናት ወድመዋል ?

<u>መልስ</u> ፣ በጣም ጉዳት የደረሰባቸው ፲፫ አብያተ ክርስቲያናት ይደርሳሉ። ጠቅላላውን ንዋያተ ቅድሳት ያጡት ፴፬ ናቸው ። በወረራው ምክንያት ከነዚህም መካከል ብዙዎቹ በዘመናዊ እቅድ የተሠሩ ፣ አንዳንዶቹ ቀደም ሲል የተሠሩና ጥንታዊ ቅርስ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናትነበሩ ።

እነዚህ በይበልጥ ቀደም ብለው የተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ቅርስ ያላቸው በመሆኑ በሀገሪቱ ላይ ታላቅ ጉዳት እንደደረሰ ለመጥቀስ እፈልጋለሁ ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ እርስዎ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ እንደመሆንዎ መጠን ፣ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ለማቋቋም ምን ርምጃ የወሰዱት አለ ወይም ደግሞ ለበላይ ባለሥልጣን ? ቢቻል ራሱ እንዲያሠራቸው ፣ባይቻል ደግሞ ከምዕመናን እስተዋጽኦ በማድረግ እንዲቋቋሙ ምን ዓይነት ጥቆማ አድርገዋል ?

<u>መልስ</u> ፣ ይህንን ብዙ ጊዜ በደብዳቤ ጠይቀናል ። የጠየቅነውም ከመስከረም ወር ጀምረን ነው ። ስለአልተቋቋመልን ከዚሁ ድረስ መጥቼ ራሴ ጥቆማ በማድረግ ከየካቲት ፲፭ ቀን ጀምሮ እያበረታታሁ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ም እያቀረብኩ በመጉትጐት ላይ ነው ያልሁት ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ አሁን እንደነገሩን አብያተ ክርስቲያናቱ ከመቋቋማቸው በፊት የምዕመናኑ ችግር እንደሚበልጥ እናምናለን ። ሆኖም እነዚህ ምዕምናን ከተቋቋሙ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ማስፈለጋቸው ስለሚታወቅ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ለማቋቋም በርስዎ በኩል ምን አስተሳሰብ አለዎት ?

<u>መልስ</u> ፣ በዚያ በኩል እርግጥ በመጀመሪያ ምዕመናኑን መርዳት አስፈላጊ ነው ። ግን ከሥፍራው ሲመለሱ በቀጥታ ጸሎት የሚያደርሱበት ቤተ ክርስቲያን ከሌላቸው እንደራሳቸው ችግር ስለሚቆጥሩት ከፍተኛ ኀዘን ሊሰማቸው የሚችለው ቤተ ክርስቲያን በማጣት መሆኑ ግልጥ ነው ። ለዚህ ቀደምትነቱን እርግጥ መንግሥት በበኩሉ ሕዝቦቹን በማቋቋም ላይ ይገኛል ። እኛ ደግሞ በቀደምትነት አብያተ ክርስቲያናቱ አብረው እንዲገኙ ካደረግን ፣ በጣም ተረዱ ማለት ነው ። ለዚህም ከዚያ ሐረር ኮሚቴ ተቋቁሞ ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ በአንዳንድ ክፍላተ ሀገር እንደምናየው ለምሳሌ ያህል በጐንደር ክፍለ ሀገር አባዳሴ ተክለ ሃይማኖት የተባለው ስለፈረሰ ቤተ ክርስቲያን የምዕመናን መሆኗ ስለታወቀች በዚያ ያሉ ምዕመናን ርዳታውን ሰጥተው የማያጠግቡ መስለው ስለታዩ ተመርጠው የመጡት ሰዎች በየክፍላተ ሀገሩ እየተዘዋወሩ ከምዕመናን ገንዘብ ይለምናሉ ። እናንተም ወደፊት አብያተ ክርስቲያናቱን በምታቋቁሙበት ጊዜ በዚህ ዓይነት ደረጃ ነው ያሰባችሁ ወይስ ደግሞ በምን ዓይነት ዕቅድ ነው ?

<u>መልስ</u> ፣ የእኛ አስተሳሰብም እርግጥ ይህን የተከተለ ነው ። ግን እኛ ኮሚቴ በየሥፍራው መርጠን ከመላክ ይልቅ ይህ ጉዳይ ወደፊትም ለሌሎች ምሳሌነት እንዲሆን በብሔራዊ አቀፍ ደረጃ ተቋቁሞ ቤተ ክህነቱ ራሱ ሰባክያኑን በየክፍላተ ሀገሩ እየላከ ከዚያም ኮሚቴ እያቋቋመ በየወረዳው በየአውራጃው ፣ በየክፍላተ ሀገሩ እንደዚህ ያለውን አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁሞ ከዚህ ማዕከላዊ ጽ/ ቤት ከፍቶ አንዳንድ መምሪያ ቁጥር ይህንን እንዲያደራጅና በዚህ ዓይነት ቢራመድ ለወደፊቱ ጥቅም ይሰጣል በሚለው ሁኔታ ነው እንጂ እኛ ለእነሱ ብቻ በመወሰን አይደለም ያቀረብነው ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ ይህንን ስታቋቁሙ በጠቅላላ የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያናት ያጠቃልላል ብላችሁ ነው ?ወይስ ደግሞ ለአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ነው ያሰባችሁት ?

<u>መልስ</u> ፣ ይህ ለወደፊቱም በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያጠቃልላል ብለን ነው ። በወረራው ምክንያት የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን ፣ ሁሉንም አንድ ላይ አጠቃሎ በወረራም ጉዳት የደረሰባቸውን በልዩ ልዩ ምክንያት የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ዓይነት ለመርዳት ይቻላል ። ወደፊትም ደግሞ ችግር በደረሰ ጊዜ ብድግ ብሎ ችግር ደርሷል ብሎ ከመለመን አንድ ቋሚ መምሪያ የወጣ እንደሁ ፣ ያ እያደራጀ ያስቀምጣል ። ያደራጀውን ችግር ለደረሰባቸው አብያተ ክርስቲያናት ይሰጣል በሚል ነው ።

<u>ጥያቄ</u> ፣ ምንም እንኳን አሁን የሶማሌ ወራሪ ጦር የሀገራችንን ዳር ድንበር ለቆ ቢወጣም ፣ ታሪክ ነውና ማስታወሻችን አይቀርም ። ለመሆኑ በጦርነቱ ጊዜ ቤተ ክህነት ወይም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች በጦርነቱ



www.ethiopianorthodox.org

ላይ የተሳተፉበት አለ ? እንዴት ነው ቢገልጹልኝ ?

መልስ ፤ አሉ ፤ ይኸውም በጦር ሠራዊቱ አበ ነፍስ ሆነው ከሠራዊቱ ጋር አብረው ተሰልፈው የነበሩት ብዙ ቀሳውስት በጦር ሜዳ ተሰልፈው ውለዋል ። እንዲሁም በዚያው ሞተው የቀሩም አሉ ። በጠላት እጅ ቆስለው የተመለሱ አሉ ። በወረራው ምክንያት አራት ካህናት ሞተዋል ። ሌሎቹ ደግሞ ዋርዶር የነበሩት ይሙቱም ይኑሩም ለማወቅ አልተቻለም እነሱም አልመጡም ። ቆስለውም በሐኪም ቤት የተኙ አሉ ። እንዲያውም ከጉዱ የመጡ አንድ ዲያቆንና ሁለት ቄሶች እየተዋጉ ነው የመጡት ። ካህናቱ ወደሐረር በሚመጡበት ጊዜ እየተዋጉ ሕዝቡን እያጽናኑ ነው የመጡት ።

ጥያቄ ፤ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸውም ሆነ ለፈረሱት አብያተ ክርስቲያናት ኮሚቴ ማቋቋማችሁን ገልጠዋል ምናልባት አሁን እርስዎ ከዚህ ከመጡ እንሥቶ በአዲስ አበባ አካባቢ እንረዳለን በማለት ቃል የገቡ እንዳሉ ቢገልጹልን ?

መልስ ፤ ኮሚቴው ከተቋቋመ ወዲህ ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ደብዳቤ ይድረሰን እንጂ እንረዳለን ብለዋል ። አሁን ዝርዝሩን ጭምር በእኛ በኩል ፴፬ አብያተ ክርስቲያናት ቢሆኑም ከባሌም ፤ ከሲዳሞም ፤ ከአርሲም የተጠቀሱ ስለአሉ ፤ እኛም ስንመለከተው ምንም እንኳን በሐረርጌ በኩል ተንቀሳቅሶ የተቋቋመ ኮሚቴ ቢሆን ፤ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደመሆኗ መጠን ፤ በሁሉም የደረሰውን ጉዳት በአንድ ዓይነት አመለካከት ማየት ስለሚገባን እንደአስፈላጊነቱ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ለእየ አብያተ ክርስቲያናቱ ታድሏል ። አሁንም የሚያስፈልገው የንዋየ ቅድሳት ዝርዝር ተዘጋጅቶ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመታደል ላይ ነው ያለው ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተስፋ ሰጥተውናል ። ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ልብስ እንረዳለን ያሉ ብዙዎች ናቸው ።

ከቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ግን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን የሚያስቀድስ ንዋየ ቅድሳት ባለምልክት ቅዳሴ ፤ ሐዲስ ኪዳን ፤ ዕጣን ፤ ዘቢብ መጐናጸፊያ ፤ የአምስት ልዑካን ልብሰ ተክህኖ ፤ አንድ ሺህ ብር ከማደሻው ጋር ነው የሰጡን ። በጠቅላላ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ሲረዱ ተነሣሥተዋል ለማለት እችላለሁ ።

(ይቀጥላል)

ነቅዓ ጥበብ ወንድም

# በ ጸ ሎ ተ ሐ ሙ ስ የ ተ ገ ኘ ው ·

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ዉብጡ የተነገረው ተፈጸመ ። እኛም ይህንን ካደረግንና ከፈጸምን በክርስቶስ ፋሲካነት ወደመተሳሰብናወደ አንድነቱ መንግሥት እንሻገራለን ። የክርስቶስን ደም በእምነት ተቀብለን በልባችን ጉበን ከረጨን ቅዱስ ጴጥሮስ እንደነገረን እንደዘንዶ ሊውጠን የሚፈልገን ጥንተ ጣላታችን ዲያብሎስ የሚአዘጋጀው ሁሉ ፈተና ያልፈናል ። የክርስቶስን ደም ጥሶ ወደሕይወታችን ሊገባ ኃይል የለውምና እውነተኛ ፋሲካችን ነው ።

በክርስቶስ ፋሲካነት የተጠቀምን በት እኛ ሰዎች ብቻ አይደለንም።የሰውን ኃጢአት ከነመከራው እየተሸከመ በየበረሃው ይወድቁ የነበሩትና በየምኩራቡ ደጃፍ በእሳት ይጋዩት የነበሩት እንስሳትም በነሱ እግር ገብቶ የሰውን ኃጢአት በመሸከሙ ከመቃጠል አረፉ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን አዲስ ሥርዓት በእንስሳትና ከእራሱ ውጭ በሆኑ ፍጥረታት ደም አትሞ ለማጽደቅ ሲፈልግ ይህ ለአዲስ ሥርዓት የሚሆን ደሜ ነው ሲል የራሱን ሕይወት መሥዋዕት በማድረግ ለዓለም ያቀረበባት ዕለት ስለሆነች እኛ ክርስቲያኖች ይህችን ቅድስት ዕለት ያዘለችውን አስደናቂ ታሪክ በአንክሮ እየተመለከትን እናከብራታለን ።

በዚች ዕለት አዲሱን ሥርዓት ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ እሱን በክርስትና ሕይወት ለሚከተሉት ወገኖቹ አስደናቂ የሆነና ዛሬም ለዓለም የታሪክ ጉዞ መንደርደሪያ የሆነ መግለጫ ሰጥቷል የተከታዩን እግር አጥቦ ልብሱንም ለብሶ ከተቀመጠ በኋላ «ያደረግሁትን ሁሉ ታስታውላላችሁን ? በማለት አስገንዝቦ «እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ ፤ ስለሆንኩም አባባላችሁ ልክ ነው ። እንግዲህ እኔ መምህራችሁና ጌታችሁ መሆኔን አምናችሁ ከተቀበላችሁ ባሪያ ከጌታውአይበልጥምና እኔ እግራችሁን እንዳጠብኩ እናንተም እርስ በርሳችሁ ይህንን ቅዱስ ተግባር ትጠቀሙበት ዘንድ ይህን ምሳሌ ሰጥቻችሁአለሁ ። ካደረጋችሁትም ብፁዓን ናችሁ » አላቸው ዮሐ- ፲፫፥፲፪—፲፯ ።

ብፁዕ የሚለው ስያሜ ከተነሣ ዘንድ በመጠኑ ለመረዳት ያህል በጸሎተ ሐሙስ የተሠራው አዲስ ሥርዓት ከክርስቲያኖች ባሕርይ ጋር ተዋህዶና ሠርጾ በግብር ሲገለጽ የሚፈልቅ እንጂ የተወሰነ አለመሆኑን ከቃሉ መገንዘብ እለብን ። «ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ኑሮ ለሁለተኛው ሥፍራ ባልተገኘም ነበር» ዕብ- ፰፥፯ እንደተገለጸው ሁሉ ያ ያረጀው ሥርዓተ ኦሪት የማያዘልቅና መፍትሔ የማይሰጥ በመሆኑ ለክርስትናው ሕይወት መመሪያ ቦታውን ለቀቁ ። በዚህም ሥርዓት ለሚመላለሱ ሁሉ ሰላምና ምሕረት ይሆናል ገላ፥ ፮፥ ፲፮» ተብሏልና እኛ የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ በጸሎተ ሐሙስ የተሠራልን አዲስ ሥርዓት መመሪያችን እንዲሆን የምናመልከው ክርስቶስ አዝዞናል ።

ይህንንም አምላካዊ ቃል ለምእመናኑ መግለጽና ማሳመን በሥራ እንዲገለጽ የማድረጉ ኃላፊነት በክህነቱ ቤት አካባቢ ያለው አስተዳደር ነው።

ስለዚህ ነው ማኅበራዊ ኑሮ መተሳሰብ ፤ መፈቃቀርና መረዳዳት የክርስቲያኖች ጠባይ እንጂ አዲስ አለመሆኑ በየጊዜው በኑሮአቸው የተጠቁ በክርስትስና ትምህርት የመጠቁ መምህራን በየቤተ ክርስቲያኑ ሲናገሩ የኖሩት ። እንግዲህ ጸሎተ ሐሙስ አሮጌው ሕግ የተደመሰሰባት ፤ አዲስ ሥርዓት የተተካባት ዘላቂ ፈውስ የተገኘባት ፤እኩልነት የታወጀባት ዕለት ስለሆነች ይህችን ዕለት እኛ ክርስቲያኖች በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜት ልናከብራት ከሌሎችም ዕለታት ይልቅ ልናገናት ይገባናል ።

አስተርአየ ጽጌ



# በሀገር ፤ ሃይማኖት አይለያየንም

ከ፱ነኛው ገጽ የዞረ

ራን በየፕሮግራማቸው እየተገኙእስከ ሴሚናሩ መጨረሻ ድረስ የተለያዩ መንፈሳዊ መዝሙሮችን በመዘመር ለሴሚናሩ ውበት ሰጥተውታል ።

የሴሚናሩ ዋና ዓላማ ፤ ስለእናት ሀገር ጥሪ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ፩ኛ ሀገር ፤ ፪ኛ/ ኅብረተሰብአዊነት ፤ ፫ኛ ሃይማኖት የፖለቲካ መሣሪያ አይሆንም ፤ ፬ኛ የእምነት ተከታዮች ለሀገራቱ የሚያቀርቡት አስተዋጽኦ በሚል ርእሶች በርከት ያሉ ምሁራን ንግግር ከማድረጋቸውም በላይ ፤ በነዚሁ ሐሳቦችና በሌሎችም ችግሮች ላይ ጉባኤው ሰፋ ያለ ውይይት አድርጓል ።

በዚሁ ወቅት የሴሚናሩ ተካፋዮች እናት ሀገራቸውን ለመርዳትና በትግሉም ተሳታፊዎች ለመሆን በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ከመነጋገራቸውም በላይ ፤ በሃይማኖት ሰበብ ብጥብጥንና መከፋፈልን የሚያስከትሉትን ወረራንም የሚፈጽሙትን አድኃርያን በአንድ ድምፅ በማውገዝ የተቃውሞ ድምፃቸውን በማሰማት የጋራ መግለጫ አውጥተዋል ።

## የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች የእናት አገር ጥሪ የሰሚናር ፍጻሜ የጋራ መግለጫ

እኛ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ፤ ለብዙ ወራት ውይይት ካደረግን በኋላ ከመጋቢት ፲፱- ቀን እስከ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓም- ድረስ የኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ በአዲስ አበባ የማዘጋጃ ቤት አዳራሽና በብሔራዊ ሸንጎ በአንድነት በሴሚናር ተሰብስበን አገራችንን ስለገጠማት ችግር ጉዳይ በወንድማማችነት መንፈስ ተወያይተን ከዚህ የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥተናል ።

፩ኛ/ የጓድ ሊቀ መንበር ወኪል የደርግ አባል ሁላችንንም የሚያስተባብር ፤ እኩልነታችንንና አንድነታችንን የሚያበሥር ንግግር በማድረግ ጉባኤያችንን ከፍተዋል ።

፪ኛ/ በጠቅላላው የክርስትና እምነት ስም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትሪያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በቃለ በረከትጉባኤውን እንዲከፍቱ ተስማምተን የአባትነት ቃለ በረከታቸውን አሰምተዋል።

፫ኛ/ ይግም ሐጂ መሐመድ ሳኒ ሐቢብ ስለኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳይ ከፍተኛ ጉባኤ ሊቀ መንበር በኢትዮጵያውያን የእስልምና ተከታዮች ስም የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል ። የክርስትናና የእስልምና እምነትመሪዎች በሴሚናሩ መክፈቻ ያደረጉት ንግግር በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ለልዩ ልዩ የእምነት ተከታዮች የተሰጠውን እኩልነት በጉልህ ያሳያል ። የአንዲት እናት ሀገር ልጆች መሆናችውንም መስክሯል ።

፬ኛ/ በሦስቱ ዕለታት የእናት ሀገር ጥሪን ምክንያት በማድረግ በአደረግነው ሴሚናር ፦

ሀ- ሀገር

ለ- ኅብረተሰብአዊነት

ሐ- ሃይማኖትና ፖለቲካ

መ- የሃይማኖት ድርጅቶች ለኅብረተሰቡ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በተሰኙ አርእስተ ነገሮች መሠረት በማድረግ በሰፊው እሳብ ለእሳብ ተለዋውጠናል ።

፭ኛ/ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ብንሆንም አምልኮአችንን ለፈጣሪያችን እንደየሥርዓታችን በነፃነትና በሰላም መግለጽ የምንችለው የአገር ድንበር ከውጭጠላት ሲጠበቅ ፤ ነፃነት ፤ ሰላምና ትክክለኛ



www.ethiopianorthodox.org

ፍትሕ ሲኖር ነው ። አገራችን ኢትዮ
ጵያ እናትነቷን ለሚያምኑ ፤ መደፈ
ሯን ለማይወዱ ፤ ክብሯን ለሚጠብቁ
ኢትዮጵያውያን ሁሉ መሆኗን እናም
ናለን ።

የየግል አገራቸውን ለሚወዱ የጉ
ረቤትና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይህን
እውነት መግለጽ እንወዳለን ። ከዚ
ህም እንፃር አንዳንድ የዓረብና የኔቶ
ባለቃል ኪዳን አገሮች የሶማሊያገዢ
መደብ አገራችንን የመውረር ፖሊሲ
በመደገፋቸውና መሣሪያም እያቀበ
ሉና ወታደሮችን እየላኩ በኢትዮጵያ
ምሥራቃዊና ደቡባዊ ክፍል በሚገኙ
ወገኖቻችን ላይ ጉዳት ስላደረሱ ሀብ
ታችንን ስላስዘረፉንና ስላጠፉ ፤ አብ
ያተ ክርስቲያንና መስጊዶችን እንዲ
ቃጠሉ ስላደረጉ ያለንን ተቃውሞበአ
ንድነት ድምፃችን በመላው ዓለም
ለሚገኙት ለሰላም ወዳጁ የክርስት
ናና የእስልምና እምነት ተከታዮች
እናሰማለን ።

የሶማሌ ገዢ መደብ መደበኛ ወታ
ደሮችና ረዳቶቻቸው በጀግናው የኢ
ትዮጵያ ሕዝብ ድል ተመተው ሸሽተ
ዋል ። ስለዚህ ከዚህ በፊት የሆነው
የድፍረት ወረራ እንዳይደገም ማንኛ
ውም መንግሥት ጣልቃ እንዳይገባ
በጥብቅ እናስገነዝባለን ። የኤርትራ
ክፍለ ሀገር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ
አካል ነው ። ስለዚህም የኔቶ መንግሥ
ታትና አንዳንድ የዓረብ አገሮች በኤ
ርትራ ጉዳይ ላይ የሚያደርጉትን
ጣልቃ ገብነት እንቃወማለን ።

፯ኛ/ ኅብረተሰብአዊነት ተጨቁኖ
ለኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነ
ትን ፤ የጋራ ብልጽግናን ፤ ትክክለኛ
ፍትሕንና ነፃነትን የሚያበሥር የኑሮ
ሥርዓት ነው ። በማንኛችንም የሃይ
ማኖት ሥርዓት እኩልነት ፤ የጋራብል
ጽግና ፤ ትክክለኛ ፍትሕ ፤ ነፃነትና
ሰላም የተደገፈ ነው ። ሃይማኖት ያለ
ነዚህ አይሠምርም ።

ስለዚህ ገራችን ኢትዮጵያ ልት
ከተለው የወሰነችውን የኅብረተሰብ
አዊነት የፖለቲካ አስተዳደር በእም
ነት እንፃር የምንቃወምበት ምክንያት
የለም ። ሃይማኖትን እንደእምነታች
ንና እንደየሥርዓታችን ይዘን ፤ ሰፊው
ሕዝብ ለኑሮው ፤ ለእድገቱ ፤ በሚበ
ጀው ሥርዓተ ማኅበር በሥነ ሥርዓት
ሲመራ እኛ እንደዜግነታችን ከኅብረ
ተሰቡ ተገንጥለን የምንታይ ሳይሆን
ገቡና በሥራ ለሚያሳዩት ኢትዮጵያ
ውያንና ኢትዮጵያውያት ሁሉ የሚደ
ረገው ርምጃ ምሕረትን ያዘለ እንዲ
ሆን እናሳስባለን በሰዎች መካከልም
እውነተኛው ፍቅር እንዲጠነክር ፤
ሰላም እንዲሠፍን የዘወትር ጸሎታ
ችን ነው ።

፰ኛ/ በብዙ የዓለም ክፍል መንግ
ሥታትና በየዘመኑ የተነሱ ኃያላን



በሰሚናሩ ላይ ከተገኙት የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች በከፊል

በአንድነት በሥራው ሱታፌ ያለን
ኢትዮጵያውያን መሆናችንን በሙሉ
ልብ እናምናለን ። )

ኢትዮጵያ በኅብረተሰብአዊነት ከተ
መራች ሃይማኖት ይጠፋል ፤ ሰላም
አይኖርም እያሉ በሃይማኖት ስም በሕ
ዝባችን መካከል ወሬ የሚነዙት ተን
ኮለኞች እንዲታገሱ እንመክራለን
ምሕረትና ቸርነት ፤ ፍቅርና ሰላም የሃ
ይማኖት ዋና መመሪያዎች ናቸው ።
በዚህ እንፃር መንግሥትም አቋማቹ
ውን እያስተካከሉ የተመለሱትን ምሕ
ረት እያደረገ ሲቀበል ስላየንና ስለሰ
ማን ደስ ብሎናል ። ለወደፊቱም በእ
ውነት ከልቡናቸው ወደኅብረተሰብ
አዊነት ሥርዓት ለሚመለሱ ፤ በሥነ
ሥርዓት ለመራመድ ቃል ኪዳን ለሚ
ለብዙ ዘመናት ሃይማኖትን የፖለቲካ
መሣሪያ ሲያደርጉት ኖረዋል ።እያን
ዳንዱ ዜጋ በአገሩ የፖለቲካ ፤ የኤኮ
ኖሚ ፤ የማኅበራዊ ኑሮና የባህል
ሱታፌ ቢኖረው በተለይ ሃይማኖትን
የፖለቲካ መሣሪያ ማድረግ ዓቢይ
ስሕተት ነው ።

በተለይ አሁን ኢትዮጵያ አሮጌውን
ሥርዓት አፍርሳ ፤ አዲስ የኅብረተሰብ
አዊነትን አመራር ለመገንባት መሠ
ረት በምትጥልበት ጊዜ ድንቁርናን ፤
ረኃብን ፤ በሽታን ማስወገድ ስትታ
ገል አገራችንን ቆርሰው ለመውሰድ
የሚያልሙ የሶማሊያ መንግሥት
መሪዎች ፤ ሃይማኖትን የፖለቲካመሣ
ሪያ ማድረጋቸውን እናያለን ። በሃይ
ማኖት ወደሚመስኋቸውም እየተሯ



ሯጡ የጥፋት መሣሪያን ሲሰበስቡ
ይታያሉ ። ይህ ዓይነቱ መንገድ የተ
ሳሳተ በመሆኑ የእስልምናን እምነት
ለማክበር ሳይሆን መሣሪያ ለማድረግ
ስለሆነ ይህንን የሞከሩት የሶማሊያ
መንግሥት መሪዎችን እንቃወማለን
በተጨማሪም ሃይማኖትህ ተደፈረብህ
እያሉ ሃይማኖትን የፖለቲካ መሣሪያ
ሊያደርጉ የሚጣጣሩትን የኢ-ድ-ሀ
የኤርትራ ተገንጣዮች ድርጅቶችን
በጥብቅ እንቃወማለን ።

፱ኛ/ አገራችን ኢትዮጵያ በመጀ
መሪያ በተፈጥሮ አደጋ በደረሰባት
ችግር በሺህ የሚቆጠሩ ልጆቿ በረ
ኃብ አልቀውባታል ። በዚያን ጊዜ
ረኃብ ያጠቃቸውን ወገኖቻችንንለመ
ርዳት ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶች
ያደረጉት አስተዋጽኦ አይዘነጋም ።
ከዚያም ወዲህ አገራችን በኅብረተሰ
ብአዊነት ለመመራት አዲስ ሥርዓት
በተካችበት ቦአሁኑ ወቅት በውስጥም
ሆነ በውጭ ጠላቶች ተነሥተውባታል

ሰላምን እንድታጣ በጦርነት ፈትነ
ዋታል ። ኤኮኖሚዋ እንዲወድቅ ታግ
ለዋታል ። በተለይም በምሥራቃዊና
ደቡባዊ ክፍል በሶማሊያ ወራሪና
ሠርጎ ገብ ወታደር በሺህ የሚቆጠሩ
ወገኖቻችን ቤታቸው ፈርሶ ፤ ንብረ
ታቸው ጠፍቶ በየመጠለያው ወድቀ
ዋል ። በሰሜናዊ ኢትዮጵያም ተመሳ
ሳይ ችግር ሕዝባችንን ገጥሞታል ።

ስለዚህ የልዩ ልዩ እምነት ተከታ
ዮች በንብረት ጉዳት የደረሰባቸውን
ወገኖች ለመርዳት ታጥቀን መነሣት
እንዳለብን ተረድተናል ። በመሠረቱ
የሃይማኖት ተከታዮቻችን በዚህ የር
ዳታ መርሐ ግብር በተቻላቸው መጠን
እንዲረዱ መንፈሳዊ መልእክታችንን
እናስተላልፋለን ።

፲ኛ/ በጋራ መግለጫችን መጨረሻ
በጥብቅ ልናሳስብ የምንወደው ፤ የለ
ውጡና የአብዮቱ ወዳጆችና ተራማ
ጆች መስለው ሃይማኖትን የሚቃወ
ሙ ፤ አብያተ ክርስቲያናትን መስጊዶ
ችን የሚደፍሩ ፤ ለመዝጋትም የሚሞ
ክሩ አልፎ አልፎ ገጥመውናል። ይህም
ከፍተኛ በዓል ተደርጎ አስተዋጽኦእን
ዲሰበስብና ለዚህም ዝግጅት ይረዳ
ዘንድ ይህ የእናት ሀገር ጥሪ አስተባ
ባሪ ኮሚቴ ሥራውን እንደቀጠለ እን
ዲቆይና ዝግጅቱንም እንዲያከናውን
ከጉባኤው ተጠይቆ በሙሉ ድምፅ



የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች ለብሔራዊ ሸንጎ በተደረገው የእናት አገር ጥሪ ሰሚናር ላይ እንደተገኙ

አፈፃጸማቸው መንግሥትን ከሕዝብ
ሕዝብን ከመንግሥት ጋር ለማጋጨት
የሚያደርጉት የተንኮል ዘዴ መሆኑ
ይሰማናል ።

ስለዚህ እነዚህን የመሳሰሉ በው
ስጠ ምሥጢር የለውጡ ተቃራኒዎች
በሆኑ ግለሰቦች መንግሥት ክትትል
እንዲያደርግና የአብያተ ክርስቲያትንና
የመስጊዶችን የነፃነት ህልውና እንዲ
ያስከብር እንጠይቃለን ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን
«ኢትዮጵያ ትቅደም»

በመጨረሻም ስለጊዜው ችግር
ማለት ስለእናት ሀገር ጥሪ ጉዳይበጦር
የተጎዱትንም ወገኖች ለማቋቋምበሚ
ደረገው ጥረት ለመተባበር ይቻል
ዘንድ በእምነት ተከታዮች ስምአንድ
አልፏል ። ስለዚህ ይኸው ዝግጅት
ወደፊት የሚደረግ መሆኑ ታውቋል።
በዚህም ስብሰባ ፍፃሜ ላይ ጊዜያዊ
ርዳታ ከአባሎቹ በተጠየቀው መሠ
ረት ወዲያውኑ ፶ሺህ ፮፻፹፱ ብር ከ፲፬
ሳንቲም (ሃምሳ ሺህ ስድስት መቶሰማ
ንያ ዘጠኝ ብር ከአሥራ አራት ሳን
ቲም) የተገኘ ሲሆን ፤ ከሀገር ፍቅር
ስሜት የተነሣ ሰዓታቸውን ፤ ወርቃ
ቸውን ፤ ካፖርታቸውንና ሸሚዛቸ
ውን ፤ እንዲሁም ሹራባቸውን ሳይ
ቀር እያወለቁ በመስጠት ስለሀ
ገራቸው ያላቸውን ከፍተኛ ስሜት
በግብር በማሳየት መልካም አርአያ
ሆነዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# መ| ቅዱስ ለሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት

## ሀ| የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት

ጥያቄውን በአጭሩ ለመመለስ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሕያውና ዘለዓለማዊ የሆነ የሃይማኖትና የማኅበራዊ ኑሮ መጽሐፍ መሆኑ ቢታወቅም ፤ ያለው መጽሐፍ ነው ። በአጭሩ እንደተገለጸው መጽሐፉ የእምነትና የማኅበራዊ ኑሮ መጽሐፍ መሆኑ ቢታወቅም ፤ ያለው ዓላማ ግን አንድ ነው ። ይኸውም በአንድ ቃል «የሰው ልጆች ደኅንነት» ነው ። ይኸው የሚፈለገው የሰው ልጆች ደኅንነት ሊኖር የሚችለውም በቅድሚያ፦

፩ኛ/ በሰውና በሰው ፤

፪ኛ/ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊኖር የሚገባው መልካም ግንኙነት ሊኖር ሲችል እንደሆነ ይኸው ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተላልፈው መልእክት ማንንም ሳይለይ ፤ ለማንም ሳያዳላ ፤ ሁሉን በእኩልነት የሚመክርና የሚገሥጽ ፤ ሁሉን እንደየሥራው የሚያጸድቅና የሚኰንን ኃይል መጽሐፍ መሆኑን መጽሐፉን የሚያነብ ማንኛውም ሐቀኛ አንባቢ ሁሉ ሊረዳው ይችላል ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት የአባትነትና ልጅነት ጠባይ ያለው እንደመሆኑ መጠን ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደየሃይማኖት መጽሐፍነቱ በአንድ በኩል በእነዚህ አባትና ልጅ መካከል የሚፈለገው መልካም ግንኙነት ሊኖር የሚችልበትን ትክክለኛ የሃይማኖት ትምህርት ሲሰጥ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሰውና በሰው መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት በትክክለኛ የወንድማማችነትና የእኩልነት ደረጃ መካሔድ እንዳለበት ከማስጠንቀቁም በላይ ፤ ይህ ዓይነቱ ግንኙነት እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል በማብራራት ፍጹም የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርትያስተምራል ።

### ለ. መጽሐፍ ቅዱስ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚሰጠው የሃይማኖት ትምህርት

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እንዲኖር ለሚፈለገው መልካም ግንኙነት መሠረቱ እምነት ነው ። ያለእምነት የሚፈለገው ዓይነት መልካም ግንኙነት ሊኖር አይችልም ። ያለዚህ ደግሞ ሕግ መንፈሳዊን የሚፈጽም እውነተኛ የደኅንነት ሰው ለመሆን እንደማይቻል ቅዱስ መጽሐፍ ያስጠነቅቃል ። የሚፈለገው እውነተኛው እምነት ይህ ነው ። የማይታየውን እግዚአብሔርን በሚታይ ሥራው ማወቅና እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ማምለክ ሮሜ ፩፥፳፩ ።

ጥንትም ሆነ ዛሬ አንዳንድ የሥነ ህላዌ ተመራማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ምርመራቸውን የሚያተኩሩት በግዙፍ ዓለም ላይ በመሆኑ የማይታይ ፤ የማይዳሰስ ፤ የማይመዘን ፤ የማይለካ ነገር ሁሉ የሌለ ነው በማለት የእግዚአብሔርንም ህልውና በዚሁ አንፃር ሊመለከቱት ይከጅላሉ ስለዚህ ጉዳይ ያላቸውን እምነትም ያለ ሌላ መንፈሳዊ ጥናትና ምርምር በዚሁ ወስነው ለማለፍ ይሞክራሉ። በዚህ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ውሳኔውን ባለመደገፍ ፤ ፈጣሪ ወይም የፈጣሪ ባህርይ በፍጡር አእምሮ ቁጥጥር ሥር የማይውል ወይም እንደጣዖት በሰዎች የፍልስፍና መሣሪያ የማይመዘንና የማይለካ ፤ ከሰው አእምሮ በላይ እንደሆነ ያስረዳል ። የእግዚአብሔር ባህርይ በሰው አእምሮ የማይጨለፍ ወይም በውሱን አእምሮ የማይወሰንና የማይመጠን ረቂቅና ምጡቅ መሆኑን አምልቶ አጉልቶ ያስተምራል ። ፩ ቆሮ- ፩ ፥ ፳—፳፪ ፤ ሮሜ ፩፥ ፳፪—፳፬ ፲፩፥ ፴፬—፴፮ ።

የሰው ልጅ ባለአእምሮ ፍጡር ቢሆንም ባለው አእምሮ የሚኖርበትን ዓለም መልክና ጠባይ ጠንቅቆ በማወቅ ገና ከፍጹምነት ደረጃ እንዳልደረሰ ራሱ ምስክር ነው ። በዚህ አንፃር እንግዲህ ማንኛውም ባለአእምሮሰው ባለው የአእምሮ ብስለት ብቻ ስለእግዚአብሔር በማወቅ ፍጹም የሃይማኖት ሰው ለመሆን እንደሚበቃ መጠበቅ አይቻልም ። ስለዚህ ከሥጋ የተወለደ ሁሉ እንደገና ከመንፈስምበመወለድ ይህን የረቀቀበትን አምላካዊ ባህርይ በመንፈስ ረድኤት አጉልቶ ለማየት ይበቃ ዘንድ በቅዱስ መጽሐፍ ይጋበዛል ዮሐ- ፫፥፮፤ ፩ ቆሮ- ፪ ፤ ፮—፲፮ ።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ዓይነት ክፍሎች ያሉት ግዙፍ መጽሐፍ ቢሆንም አጠቃላይ ዓላማውአስቀድሞ እንደ ተገለጸው፤ የሰው ልጆች ደኅንነት ብቻ ነው ። ምንጊዜም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጆችን የሥቃይ ኑሮ አይደግፍም ። በሰው ልጅ ሕያውነትና ዘለዓለማዊነት እንጂ ከንቱነትና ኢምንትነት አያምንም ። አያሳምንም ። የሰው ልጅ ከኀሣር ወደክብር ከሐዘን ወደስታ ፤ ከኩነኔ ወደጽድቅ፤ ከሞት ወደሕይወት እንዲሸጋገር እንጂ በየትኛውም ዓለም የገሃነም ኑሮን እንዲኖር አያዝም ። መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጠው የሃይማኖት ትምህርት ብዙ ጊዜ በሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ያተኮረ ቢመስልም አንድ ዓይነት መጽሐፍ አይደለም ። ለሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስበውን ያህል እንዲሁ ለሥጋዊው ሕይወትም ያስባል ። ይህ ከሆነ ዘንድ በአንድ በኩል የሰው ልጅ በየጊዜው ሕይወተ ነፍስ ሕይወተ ሥጋ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር እንዲመገብ ሲጋበዝ በሌላ በኩል ደግሞ ነፍስ ያለ ሥጋ እንደማትቆምና ማንኛውም ሰው ያለ ዳቦ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ እንደማይኖር ያስጠነቅቃል ። የሃይማኖት ሰዎች ፍጹም የሥራም ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ የማይሠራ አይብላ ሲል ያውጃል ። ስለዚህ የዓለም ኑሮ መቃናትም በሚያስተምረው ቃል በዚህ ዓለም ላይ ለሰው ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔርም ለመሆን ፈቃድ የሚፈጽም ፍጹም የሃይማኖት ሰው ለመሆን ቢፈልግ የሚያየው ወንድሙን መልካም ፈቃድ የሚፈጽም ፍጹም የማኅበራዊ ኑሮ ሰው መሆን እንዳለበት ያረጋግጣል ።

### ሐ/ መጽሐፍ ቅዱስ በሰውና በሰው መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚሰጠው የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርት

በመጽሐፍ ቅዱስ የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርት ትንተና ሰውን መውደድ እግዚአብሔርን መውደድ ፤ እግዚአብሔርንም መውደድ ሰውን መውደድ ስለሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት በሰውና በሰው መካከል ካለው ግንኙነት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ለዚህም ዋናው ምስክር ይህ ነው ። «ወንድሞች ሆይ ! እርስ በእርሳችን እንዋደድ ፍቅር የሌለው ሰው እግዚአብሔርን አያውቅም ፤ እግዚአብሔርን ከቶ ማንም ያየው የለም ። እርስ በእርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ። ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ይሆናል ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው።የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ፤ የማያየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወድድ ይችላል ? » ፩ ዮሐ- ፬፥፯—፳፩ ።

በዚህ ኃይለ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች ሊያስረዳ የሚፈልገው ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ አንድም ሁለትም እንደሆኑና እግዚአብሔር ያጣመረውንም ሰው ሊለይ እንደማይችል ነው ።

ይህ እንዲህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱስ መጽሐፍ በሰዎች መካከል መልካም ግንኙነት ይኖር ዘንድ ለማንኛውም የኅብረተሰብእ አባል የበኩሉን የማኅበራዊ ኑሮ መመሪያ ሲሰጥ «ሌላው ለአንተ ሊያደርግልህ የምትፈልገውን አንተም ለሌላውአድርግ ። ሌላው በአንተ ላይ ሊያደርስብህ የማትፈልገውን አንተም በሌላው። ላይ አታድርግ» ይላል ማቴ- ፯ ፤ ፲፪ በዚህም አባባሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የማኅበራዊ ኑሮ መጻሕፍት ብዙ ዓምድና ብዙ ገጽ የሚፈጅባቸውን የማኅበራዊ ሕግ ትንተና በሁለት ዓረፍተ ነገሮች ብቻ አሟልቶ ለመግለጽ የቻለ በእርግጥ ታላቅመጽሐፍ መሆኑን ያረጋግጣል ። ይህ በመሆኑም ዓለም በዚህ ታላቅ መጽሐፍ መመሪያነት ሲገለገል እንደኖረ ወደፊትም ይኖራል ። ስለዚህ ትክክለኛ የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓት ይታነጽ ዘንድ ለሚደረገው የተቀደሰ ትግል የመጽሐፍ ቅዱስ መሣሪያነት ተወዳዳሪ የሌለው ጥንታዊና ዘመናዊ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል ።

በቅድሚያ እንደተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዋና ዓላማየሰው ልጆች ደኅንነት እንደመሆኑ መጠን እውነተኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለሰው ልጅ እኩልነትና ነፃነት ፤ ስለ ፍትሕና ርትዕ መታገል ከጀመሩዜ ጊው ቅርብ አይደለም ። በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት አልፈዋል ። ከሆነ ጀምሮ ዓለም ከግፍና በደል ርኩሰት እንድትነፃ በየጊዜው የትግል ድምፃቸውን ያረሙበት ጊዜ ሳይኖር በነቢይነት በሐዋርያነትና በሰማዕትነት ታግለዋል ። ለአመኑበት ትክክለኛ ዓላማም እስከ ሞት ድረስ የታመኑ ሁነዋል ። እነዚያ የፍትሕና ርትዕ ሰማዕታት ለዚህ መስተጋድልነት የበቁት እንዲያው በባዶ ጉልበት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ባስታጠቃቸው የመንፈስ ሰይፍ ነበር ። ለዚህም ዋናው ምስክር ከክርስቶስ ልደት በፊትም ሆነ በኋላ የተነሡት ነቢያትና ሐዋርያት የትግል ታሪክ ነው አሞፅ ፰-፬ ፤ ኢሳ- ፶፰፥፮ ፤ ኤር- ፯፥፩-፲፩ ።

ይልቁንም ለብዙኃን ቤዛ ንጹሕ ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ጌታችን ኢየሱስ ፤ ስለዚህ ዓለም ተልዕኮው ዋና ዓላማ በሰጠው ማረጋገጫ «የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ፤ ለድሆች የምሥራችን ፤ ለታሠሩት መፈታትን ፤ ለዕውሮች ማየትን እሰብክ ዘንድ ። የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ ። የተወደደችውንም የጌታ ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ሉቃስ ፬፥፲፱- የሚል ግልጽ የሆነቃል በመናገሩ በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የእምነትና የማኅበራዊ ኑሮ መጽሐፍ መሆኑ በገሃድ ተረጋግጧል

እንደሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ግዙፍ መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን «መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው ? አገልግሎቱስ ? » የሚለውን ዓቢይጥያቄ

ወደ፲፰ኛው ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የሰባት ዓመት ተጋድሎ የሥራ ውጤት

የተባለውንም ተጋድሎ ፈጽሞ የሥራ ውጤት ያሳየው ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው። ስለተጋድሎው ከመናገራችን በፊት ትውልዱን መናገሩ ሥራውን ተጨባጭ ያደርገዋል። የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዘሮንቶስ ሲሆን እናቱ ቲዮብስታ ነች ፣ እሷም ፍልስጥኤማዊት ናት ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ የተወለደበት ዘመን በ፪፻፺ ዓ/ ም/ ነው ። የተወለደባትም አገር ቀጰዶቅያ ትባላለች ።

ቀጰዶቅያም በትንሹ ምሥራቃዊ እስያ (እንደዛሬ አጠራር መካከለኛው ምሥራቅ) ትገኛለች ። ከሮም ገናና መንግሥት በፊት በፋርስ መንግሥት ሥር ነበረች ። ጊዮርጊስም የፋርስ ሰማዕት የሚባለውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል ። ይህችን አገር ግሪኮችም ፣ ሮማውያንም ቅኝ አገር አድርገዋት እንደነበር ታሪክ ያብራራል ።

በዚህ አኳኋን አንዳንድ ሰዎች ጊዮርጊስን የግሪክ ተወላጅ ነው ሲሉ ፣ ሌሎችም ደግሞ የሮም ተወላጅ ነው ይላሉ ። ጥቂቶችም የእንግሊዝ ዜጋ ነው ይላሉ ። ለዚህ ሁሉ ከአፈ ታሪክ በቀር ብዙ ጊዜ ተመርምሮ እስከአሁን ድረስ በቂ ማስረጃ አልተገኘም ከዚህ የተነሣ ጊዮርጊስን የዚህ አገር ተወላጅ ነው ፣ የዚያኛው አገር ዜጋ ነው የሚል አነጋገር ቢሰጥ አያስደንቅም ። ምክንያቱም የሠራን ሰውና ጀግናን ማንም ሰው የሱ ዜጋ እንዲሆን ስለሚፈልግ ነው ።

ይሁን እንጂ በዚያን ዘመን ወታደርነት ተፈላጊ ሙያ ስለነበር ጊዮርጊስም ወታደር ሆኖ ብዙ ጀብዱ ፈጽሟል ። በወጣትነቱ የውትድርና ሥራ እንደሠራ በግሪክ ፣ በኮብቲክና በሶርያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተጽፏል ይልቁንም በስንክሳርና በራሱ ገድል ተጽፏል ። ጥቂትም ጊዜ በወታደርነት ከሠራ በኋላ የክርስቶስ ወታደር ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ጀመር

በዚህ ሥራው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት ስለ ክርስትና ሃይማኖት ብዙ ተጋድሎ አድርጓል ። ወንጌልንም አስተምሮ ብዙ ያላመኑ ሰዎችን ወደ ክርስትና እምነት መልሷል ። ገድሉ እንደሚለው ቢሩታዊት የተባለችውን ልጃገረድ ደራጎን ለተባለው ዘንዶ ግብር እንድትሆን ቀርባ ሳለች ፣ ዘንዶውን በጦር ወግቶ ገድሎ እሷን ከመበላት አድኗታል ። ይህንም ዘንዶ ሕዝቡ ሁሉ አምላክ አድርገው ስለሚያመልኩት በቀን በቀን አንዳንድ ከወንድም ፣ ከሴትም ወጣት እየመለመሉ ያቀርቡለት ነበር ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተንታኞች ግን በ፲፪ኛው ክፍለዘመን የተጻፈው ታሪክ አንዲት ልጃገረድን ከደራጎን እንዳዳነ የተመዘገበውን ጽሑፍ ልዩ ትርጉም ሰጥተውታል። አባባላቸውም በዘመነ ሰማዕታት ከ፪፻፹፬ እስከ ፫፻፳ ዓ· ም· ድረስ በክርስቲያኖች ሴቶች ልጆች ላይ ብዙ ግፍ ይፈጸም ነበር ። ከዚህም የተነሣ አንድ ግፈኛ መኰንን በአንዲት ልጃገረድ ላይ ግፍ ሊፈጽምባት ሲሞክር ጊዮርጊስ ደርሶ ገድሎ ልጃገረዲቷን ከሞት አዳናት ።

ከዚህ በኋላ ይህ ታሪክ በምሳሌያዊ አነጋገር ቀረበ ። ነገር ግን ከጊዮርጊስ ሥዕል ጋር የሚታየው ደራጎን በዓለም ላይ የሌለ አውሬ ነው ተብሎ ተገምቷል ። በግልጥ አነጋገር ዮሐንስ በራዕዩ እንዳየው ዘንዶ ምሳሌያዊ መልክ ነው የሚል ነው ። ይህንንአባባል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ይቃወሙታል ።

ጊዮርጊስ ደራጎንን ከገደለበኋላ ሥራው ባገር ሁሉ ታወቀ በዚያን ዘመን ክርስቲያኖች በየቀኑ እየተገደሉ በየሜዳው ይጣሉ ስለነበር ፣ እየተዘዋወረ ክርስቲያኖችን ያጽናናቸው ነበር ። የግፍ ሞት ከሚፈጸምበት አደባባይ የደከሙትን ሽማግሌዎችን አሮጊቶችን እንዳይፈጁ በፈረስወደ ሌላ ሥፍራ ያሸሻቸው ነበር ። ፈረሰኛው ጊዮርጊስም የሚያሰኘው ይህ ነው ።

ስለ ክርስትና እምነት የተጻፉትን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ንዋየ ቅዱሳትንም በየዋሻውና በየመሬቱ ሥር እየደበቀ ያስቀምጥ ነበር ። በጠቅላላ በተፈጥሮና በትምህርት ችሎታ በእግዚአብሔርም ፀጋ መንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ስለነበር ፣ ስለእውነት ፣ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ፣ ስለ ሰላም ፣ ስለእኩልነት ፣ ስለፍትሕ ታግሏል ። ይህም ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ስጦታዊ ታሪክ ወርቃዊ ስጦታ ተአምራዊ ተብሏል ። እርግጥም እውነትና ፍትሕ በጠፋበት በዚያ ዘመን ስለእውነት ፣ ስለፍርድ፣ ስለ ሰላም መመስከር ተአምር ሊባል ይቻላል ።

ከዚህም የተነሳ ከ፪፻፸፫—፫፻፴፱ ዓ· ም· የነበረው የቤተ ክርስቲያን አባት የሆነው አውሳብዮስ ዘቂሳርያ ጊዮርጊስ ብርቱና ሰማዕት እንደሆነ መስክሮ ጽፏል ። የአውሳብዮስ መጽሐፍ ፰ ፡ ፭ ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ብዙ ዘመን ስለ እምነቱ ፣ ስለአገሩ ነፃነት ፣ ስለ እኩልነት ፣ ስለ ሰላም ፣ ስለፍትሕ ከታገለ በኋላ የመንፈስ አርበኛ እንደመሆኑ መጠን ፣ የመከራውን ሸለቆ ተሻገረ ፣ ከሕይወትም ወደብ ደርሶ ምዕመናን እየተያዙ በሚገደሉበት በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት በ፫፻፫ ዓ· ም· ሚያዝያ ፳፫ ቀን ልዳ በሚባለው አገር] በሰማዕትነት አርፏል ። በዚህም ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች ተስማምተውበታል ። ስለዜና ቅድስናው ከላይ በተገለጸው መሠረት ቅዱስነት ወይም ቅድስና ያለ ሥራ ሊሰጥ ባለመቻሉ ከነ አውሳብዮስ ዘመን ጀምሮ የጊዮርጊስ የሥራ ታሪክ ጥናት ተጀመረ ። ቅዱስ የተባለውን ስም ለማግኘት በሥራና በአካሄድ ክርስቶስን መምሰል እንደሱ ሌላውን ማገልገልና ለራሱ ሳይሆን ስለሌላው መኖር ያሻል ። ስለሌላው ተላልፎ መሞት መከራን መቀበል፣ መስቀልንም መሸከም በሰው ፊት መመስከርና ራስንም መካድ ያስፈልጋል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስም ይህን ሁሉ ተግባር ሠርቶ በመገኘቱ ብዙ ምስክር ተገኘለት ። ስለዚህ በ፭ተኛው መቶ ዘመን በደቡብ ሶሪያ በምትገኘው ኤድራ ወይም(ይድራስ)በተባለች ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የቤተ ክርስቲያን አባቶች እውነተኛ ሰማዕትነቱንና ቅድስናውን በጉባኤ አጽድቀው ውሳኔውን ለሕዝብ አስተላለፈዋል ። በ፲፻፺፰ ዓ· ም· ደግሞ በአንጾኪያ በተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ላይ ክርስቲያኖችን ሲረዳ በራዕይ እንደታየ ተነገረና ስሙ ገናና መሆን ጀመረ ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በእንግሊዝም ሀገር ስሙ ጥሩ ሰማዕት ነው «የእንግሊዝ መንግሥት ጠባቂ» በሚል የቅጽል ስም ይጠራል ። ከ፰ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በእንግሊዝ አገር ዝነኛ እንደሆነ እንግሊዞች ያምናሉ ። በ፩ሺ፰፻፩ ዓ· ም· ገድሉ በእንግሉ ሳክሰን ቋንቋ ተተረጎመ በዚሁ ዓ· ም· በስሙ ቤተ ክርስቲያን ታነጸ ። በ፲፪፻፹፪ ዓ· ም· ደግሞ በኦክስፎርድ በተደረገው ሲኖዶስ በዓሉ ከንዑሳን በዓላት ገብቶ እንዲቆጠር ተወሰነ ።

በ፲፫፻፵፰ ዓ· ም· ፫ኛው ኤድዋርድ በነገሠ ጊዜ መደቡ ነጭ ሆኖ ቀይመስቀል ያለበት ባንዲራ ተሠርቶ የተጋዳዩ ጊዮርጊስ ባንዲራ ተባለ ። ይህም ለምድር ጦርና ለባሕር ኃይል ሠራዊት መለዮ እንዲሆን ተሰጠ ። የእንግሊዝ መንግሥት ጠባቂ የሚል የክብርስም የተሰጠው በዚሁ ዘመን ነው ። እንደገና በ፲፬፻፲፭ ዓ· ም· በዓሉ ከዓበይት በዓላት ጋር እንዲቆጠር ተወሰነ ።

ዛሬም ቢሆን በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የዘወትር የጸሎት መጽሐፍ ላይ የሚገኘው (ኮመን ታሪ) የበዓላትም ቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ሚያዝያ ፳፫ ቀን የጊዮርጊስ የሞቱ መታሰቢያ ቀን እንደሆነ ያመለክታል።ለዕለቱም ተስማሚ የሆነ ምንባብ በዚሁ የጸሎት መጽሐፋቸው ተዘጋጅቷል። ይሁን እንጂ አከባበሩ ሥራ ፈቶ በመዋል አይደለም ። በዚያም ሆነ በዚህ ጊዮርጊስ በእንግሊዝ አገር ታላቅ የክብር ስም አለው ።

ከላይ የተገለጸው የቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪክ የተገኘው ፡—

፩- ዲክሽነሪ ኦፍ ክርስቲያን ባዮግራፊ ቮልዩም ፪ ገጽ ፯፻፵፭—፯፻፵፰ ፣
፪- በሬይኒካ ኢንሳይክሎፕዲያ ገጽ ፩ሺህ ፯፻፰፰ ፣
፫- ኦክስፎርድ ዲክሽነሪ ዘቤተ ክርስቲያን ፣
፬- ሚስተር ዴቪድ እስኪዩኑ የታሪክ ፕሮፌሰር ፣

ታሪኩ ከነዚህ የተገኘ ሲሆን እነዚህም መጻሕፍት ቢሆኑ ታሪኩን ከማብራራት በቀር ጊዮርጊስ የእንግሊዝ ዜጋ ነው አይሉም ።

በኢትዮጵያም ቅዱስ ጊዮርጊስስመ ጥሩ ሰማዕት ነው ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ በራዕይ እንደታየውና እራሳቸውም ጣሊያኖችም ቢሆኑ አንድ በፈረስ የተቀመጠ ጀግና ሰው ሠራዊታችንን የጎዳው እሱ ነው እያሉ ጊዮርጊስ መሆኑን መስክረውሊታል ።

ይህ ከሆነ ምዕመናን የሆን ሁሉ ፣ ለቅዱስነት ፣ ለሥራ ፣ ለክብር የተጠራን መሆናችንን መርሳት አይገባንም ሩጦ ካልቀደሙ ሽልማት ፣ መከራን ካልተቀበሉ ጸጋ ፣ ካልተጋደሉ የሥራ ውጤት ፣ ካልተዋጉ የሀገር ነፃነት ፣ ሃይማኖት ካልጠበቁ ክብር ፣ ካልሠሩ ዋጋ አይገኝምና ሁላችንም እንታገል እንሥራ ።

በዚህ አኳኋን በሰዎች ፊት ስለጌትነቱ ፣ ስለአምላክነቱ ፣ ስለስሙ ልንመሰክር ይገባናል ። «ሁሉም የእናንተ ነው ፣ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ፣ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው» ሐዋርያው ስለሚል እየታገልን የሥራ ውጤታችንን እናሳይ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---

## መጽሐፍ ቅዱስ…

ከ፲፯ኛው ገጽ የዞረ

በዚህ አጭር ትንተና አጠቃሎ ለመመለስ ስለሚያዳግት፣ ከዚህ ላይ በአጠቃላይ ለማስረዳት የሞከርኩት መጽሐፍ ቅዱስ የእምነትና የማኅበራዊ ኑሮ መጽሐፍ እንደሆነና ይህ በመሆኑም እያሌ የእምነትና የማኅበራዊ ኑሮሰማዕታትን ለዓለም ያበረከተ ታላቅ መጽሐፍ መሆኑን ነው ።

ክርስቶስ ስለሰው ሙቷል ተነሥቷል ። ይህ ስለሆነም ማንኛውምሰው ይህን አርአያ ተከትሎ ሰውንና እግዚአብሔርን በማገልገል በእምነቱ እውነተኛ የማኅበራዊ ኑሮ ሰማዕት ይሆን ዘንድ ማስተማር የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ተፈላጊ ነው።በዚህም ቅዱስ ተልዕኮው መጽሐፍ ቅዱስ የብዙኃን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሆነ ይኖራል ።

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን





www.ethiopianorthodox.org

# የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ገዳማትን

# በማቋቋም ረገድ ምን ሠራ?

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጀምሮ ብዙ ልማት ነክ ሥራዎችን ለቤተ ክርስቲያንና ለካህናት ፤ ለምእመናንና በጠቅላላውም ለኅብረተሰቡ እንዳበረከተና በማበርከትም ላይ ያለ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ይኸውም ካህናትን በማሠልጠን ለኅብረተሰብኡና ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ልማት ነክ ዕቅዶችንና የጎጆ እንዱስትሪዎችን በማቋቋምና በማገዝ የተቻለውን ያህል ሲረዳና ለመርዳትም ሲሞክር ቆይቷል ።

ለምሳሌ ያህል ፤ ለአዋሽ ሕዝብ የነበረበትን ከባድ የውሀችግር በኤሌክትሪክ ኃይል ለማስወገድ በተደረገው ጥረት ፲ሺህ (አሥር ሺህ ብር) በመለገሥ ያለውን ተባባሪነትና በጎ ፈቃድ አሳይቷል ። ይህ ለምሳሌያህል ተጠቀሰ እንጂ ይህንንና ይህን የመሳሰሉ ብዙ መልካም ተግባራት ፈጽሟል ። በሀገሪቱም በደረሰው የድርቅ ችግር የተነሣ ለተጎዱ ወገኖቻችንዕርዳታ በማድረግ የተቻለውን ያህል ተሳትፏል ። በዛ ላሉ ገዳማትም ለምግብ የሚያገለግሉ ርዳታዎች ለግሷል።መለስተኛ እንዱስትሪዎችም እንዲቋቋሙ ረድቷል ።

በአሁኑ ጽሑፋችን ኮሚሽኑ ገዳማትን ለማቋቋም ከፈጸማቸው ተግባራት ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን ።

## ፩· የዝቋላ አቦ ገዳም

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም የሚገኘው በሸዋ ክፍለ ሀገር በየረርና ከረዩ አውራጃ በዝቋላ ኮረብታ ላይ ነው ። በገዳሙ ውስጥ በዛ ያሉ መነኮሳትና ዓቅመ ደካማዎች ይገኛሉ ።

ገዳሙ ቀድሞ ይተዳደር የነበረው ከመሬት በሚገኝ ጥቅም ሲሆን፤በኋላ ግን የገዳሙ ንብረት ከሆነው የእህል ወፍጮ ኪራይና ከምእመናን በሚገኝ ርዳታ ነበር ።

ሆኖም የእህሉ ወፍጮ ከ፲፰ ዓመታት በፊት ተተክሎ ለረዥም ጊዜሲያገለግል ቆይቶ ከባድ ብልሽት ደርሶበት ለ፮ ወራት ያህል አገልግሎቱን በማቋረጡ በገዳሙ ላይ ከባድ ችግር ደርሶ ነበር ። ይኸውም እንደኛገዳሙ ከወፍጮ ኪራይ የሚያገኘው ገቢበድንገት በመቋረጡ ሲሆን ፤ ሌላውደግሞ ወፍጮው ተበላሽቶ ከጥቅም ውጭ በነበረበት ወቅት በገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት የ፰ ሰዓት ደርሶ መልስመንገድ እህል በአህያ በማጓጓዝ ለማስፈጨት የተገደዱ መሆናቸው ነበር።በወፍጮው ይገለገሉ የነበሩት የአካባቢው ምእመናን በዚሁ ሳቢያ ችግር ደርሶባቸው እንደነበር መገመቱከባድ አይሆንም ።

የገዳሙ አስተዳዳሪ በገዳሙ ላይ የደረሰውን ይህን ከባድ ችግር አስመልክተው ርዳታ ይገኝ ዘንድ ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት በማመልከታቸው ጉዳዩ አሳሳቢና አጣዳፊ መሆኑን በመገንዘብ ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት አንድ ሰው በአስቸኳይ ወደገዳሙ ተልኮ ሁኔታውን ተመልክቶ ሪፖርት እንዲያቀርብተደርጓል ።ኮሚሽኑም በቀረበው ሪፖርት መሠረት በጉዳዩ ላይ ተነጋግሮበት ገዳሙ ያለበት ሁኔታ ኮሚሽኑ በአሁኑ ጊዜ በገዳማትና በአድባራት ራስአገዝ የልማት ሥራዎች እንዲቋቋሙ ከሚያደርገው ጥረት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በማግኘቱና ይልቁንም የወፍጮው በሥራ ላይ መዋል ገዳሙን ብቻ ይሳሆን የአካባቢውንም ሕዝብ የሚጠቅም መሆኑ በመታመኑ ፭ሺህ፰ ብር ከ፰፭ ሳንቲም ወጭ በማድረግ ወፍጮው ተጠግኖ የተለመደ አገልግሎቱን እንዲሰጥ አድርጓል ።



መነኩሴው በልማት ሥራ ሲሳተፉ



ስለዚህም በተለይ በገዳሙ አባላት እንደዚሁም በአካባቢው ሕዝብ ላይ በወፍጮው መሰናከል የተነሣ ደርሶባቸው የነበረው ከባድ ችግር በአሁኑ ጊዜ ሊቃለል ችሏል ።

## ፪ አንጋራ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ፤

የአንጋራ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የሚገኘው በጐንደር ክፍለ ሀገርበጣና ሐይቅ ውስጥ ሲሆን ዙሪያውን በውሀ የተከበበ በመሆኑ በታንኳ አማካይነት ካልሆነ በስተቀር ከቦታው መድረስ አይቻልም ።

የመሬቱ ስፋት ፺ ሄክታር ሲሆን ፤ ከዚህ ውስጥ ለእርሻ አመቺ ሆኖ የተገኘው ፪ ሄክታር ተኩል ብቻ ነው ። የቀረው ግን ድንጋያማና ለእርሻ ምቹ ያለመሆኑን ከቦታው ተገኝቶስለ ገዳሙ ሁኔታ ጥናት ያካሔደው ቡድን ከሰጠው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል።

የጥናቱ ቡድን የተውጣጣው ከክፍለ ሀገሩ የእርሻና ሕዝብ ማሥፈር ወኪሎች ፤ ከአዝርዕት ጥበቃና ኤክስፐርቶች ሲሆን ፤ የአንጋራ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የሚገኝበትን አካባቢ በማጥናት ራስን በራስ መርዳት የሚያስችል ዘላቂ የእርሻ ልማት እንዴት ማቋቋም እንደሚቻል አጠር ያለጥናት አቅርቧል ።

ቡድኑ በጥናቱ መሠረት በገዳሙ ውስጥ የሚገኙትን መነኮሳት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያቋቁሙና ራሳቸውን ሊያስችላቸው የሚችል የእርሻ ልማት ለመትለም የሚያበቁትን ሐሳቦችአቅርቧል ።



ካህኑ ዶማቸውን ይዘው ሰብላቸውን ሲኮተኩቱ

በዚህም መሠረት የቡድኑ አባሎች የአየሩን ጠባይና ከአሁን ቀደም በአካባቢው ይበቅሉ የነበሩትን አዝርዕትና አትክልት በመመርመር በገዳሙ ወደፊት ቡና ፤ ብርቱካን ፤ ማንጎ ፤ ፓፓያና ጥጥ ቢተከሉ ጥሩ ውጤት እንደሚገኝ እምነታቸውን ገልጸዋል።

ይሁን እንጂ በጥናቱ መሠረት የተጠቀሱት አትክልት ዘወትር እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ከመሆናቸው በላይ ፤ ውጤታቸው ቶሎ ላይታይ እንደሚችልና ነገር ግን አንዴ ፍሬ መስጠት ከጀመሩ ጥሩ ውጤት እንደሚገኝባቸው የማያጠራጥር መሆኑ ተጠቁሟል ። ሆኖም የገዳሙ የገቢ ምንጭ ሁልጊዜ እንዳያቋርጥ ከተፈለገ የጓሮ አትክልትም መትከል እንደሚቻል ተጠቁሟል ። ስለዚህም ለአየሩ ጠባይ የሚስማሙ እንደ ቲማቲም ፤ ጥቅል ጐመንና ካሮት የመሳሰሉትን በመትከል ጥሩ ገቢ ለማግኘት ከመቻሉም በላይ ፤ ለመነኮሳቱ ተመጣጣኝ ምግብ ለማዘጋጀት እንደሚረዳ ታምኖበታል

ከተደረገው ጥናት ለመረዳት እንደተቻለው ምንም እንኳ ገዳሙ በጣና ሐይቅ የተከበበ ሆኖ ቢገኝም ፤ የመሬቱ የተፈጥሮ አቀማመጥና ሁኔታ ለመስኖ አመቺ ባለመሆኑ ከሐይቁ ውሀ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም ። ዳሩ ግን የእርሻው ሥራ በሚገባ እንዲካሔድ ከተፈለገ ፤ የማያቋርጥ ውሀ ማግኘት ያስፈልጋል።የማያቋርጥ ውሀ ለማግኘት ደግሞ በሞተር ኃይል የሚሠራ የውሀ መሳቢያ ፓምፕ መኖር አለበት ። በተጨማሪም ውሀውንከተፈለገው ቦታ ለማድረስ የሚያስፈልጉት ቧንቧዎችና የውሀ ማጠራቀሚያ ለእርሻው ሥራ የሚያገለግሉት የእርሻ መሣሪያዎች ፤ የተባይ ማጥፊያ መድኃኒቶችና ልዩ ልዩ አዝርእትማግኘትና በቅድሚያ ማዘጋጀት ተገቢ መሆኑ ቢታወቅም ፤ እነዚህን ለማሟላት ገዳሙ ዓቅም በማጣቱ የርዳታው ጥያቄ ለልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን እንዲቀርብ ተደርጓል።

ኮሚሽኑም በቀረበለት የጥናት ውጤት ገዳሙ ያለበትን አስቸጋሪሁኔታና ወደፊትም ሊያጋጥመው የሚች



www.ethiopianorthodox.org

ለውን ከባድ ችግር በፍጥነት በመረዳትና ፦—

ሀ- የእርሻው ልማት ቢቋቋም መነኮሳቱን ለዘለቄታው የሚረዳና የሚያቋቁማቸው ፤ እንደዚሁም ራሳቸውን የሚያስችላቸው ዕቅድ መሆኑን ፤

ለ- የእርሻው ልማት መቋቋምና የውሀው መሳቢያ ሞተር በዚያገዳም መኖር ለአካባቢው ሕዝብምሳሌ ሊሆን ከመቻሉም በላይ ለኤኮኖሚው እድገት ሊረዳ እንደሚችል በመገንዘብ ጥያቄውን ተቀብሎ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የልማት ክፍል ከ፫ እስከ ፭ ገዳማትን በሙከራ መልክ ለማቋቋም ከተመደበው የርዳታ ገንዘብ ወጭ ሆኖ አስፈላጊዎቹ መሣሪያዎች በአስቸኳይ ተገዝተው እንዲሰጡ አድርጓል ።

በዚህም መሠረት ገዳሙን ለማቋቋ በርዳታ የተፈቀደው ጠቅላላ ገንዘብ ፲ሺህ ፬፻፳፮ ብር ከ፰፭ ሳንቲም ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ፩ሺህ ፰፻፺ ብር አንድ በናፍጣ የሚሠራ የውሀ መሳቢያ ሞተር ተገዝቶበታል ። በቀሪው ደግሞ፦—

ሀ- አንድ ትልቅ የውሀ ማጠራቀሚያ ቢርካ እንደሚሠራ ፤

ለ- የቧንቧና የእርሻ መሣሪያዎች ፤

ሐ- የተባይ ማጥፊያ መድኃኒት ፤ ልዩ ልዩ አዝርዕቶችና አታክልት እንደሚገዛበት ታውቋል ።

ይህ ገዳም የደረሰበትን ችግር በቅርብ በመመልከት ሁኔታው እንዲጠና ያሳሰቡትና ተገቢውም ርዳታ እንዲገኝ ጥናቱን ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት ያቀረቡት የጐንደር ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ናቸው ።

ኮሚሽኑ ገዳማትን ለመርዳት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ባገኘው ገንዘብ የረዳው ይህንን ገዳም ብቻ አይደለም ። በሌሎችም ገዳማት ይህንኑ የመሰሉ ራስ አገዝ ሥራዎች እንዲቋቋሙ ተገቢውን ርዳታ አድርጓል ። ወደፊትም ይህንና ይህን የመሳሰሉ ራስ የሚያስችሉ ዕቅዶችን በየገዳማቱ ለማቋቋም የሚተጉትን ለመርዳት በመጣጣር ላይ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ በደስታ ይገልጻል ።



ካህናቱ ሰብሉን ውሃ ሲያጠጡ

## ክርስቲያን ወይስ ቤተ ክርስቲያን ?

በእኔ አባባል ክርስቲያን ማለትበእምነት ደረጃ ሕዝበ ክርስቲያን ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ማለት ደግሞ ድርጅቱ ወይም አስተዳደሩ ነው ። በርከት ካሉ ዘመናት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አቅዋምዘመኑ በሚፈቅደውና ለአማኙ ሕዝብአመቺ በሆነ መንገድ ሥርዓቱ እንዲሻሻል ከብዙ ግለሰቦች ተደጋግሞ መጠየቁ አይካድም ።

በቅድሚያ መሻሻል ያለባቸውም ሥርዓቶች በእኔ አስተያየት ፤ ስለበዓላት ፤ ስለካህናት አለባበስ ፤ ስለጸሎት (በተለይ ጸሎተ ማኅበር) ሲሆኑ፤ከነዚህ ተነጥሎ የማይታየው ሌላ ሥርዓት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎትና የጊዜ ጉዳይ ነው ። እነዚህኑ አንቀጾች ምእመናኑ የተሰላቹባቸው በመሆናቸው ቅድሚያ እንዲያገኙ አልኩ እንጂ ፤ መሻሻልስ የሚያስፈልጋቸው ሌሎችም በብዛት አሉ።መደረግም የሚገባው ማሻሻያ ፤ መመሪያችን ከሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውጭ እስካልሆነ ድረስ ሕዝቡ በሚወደውና ሕዝቡ በሚፈቅደው ዓይነት ሆኖ ካለንበት ኅብረተሰብእ ጋር መዛመድና መራመድ ይኖርበታል ።

ለምሳሌ ፤ የሕዝቡ ኤኮኖሚ እንዳያድግ ከሚያደርጉት ባህሎች አንዱ የበዓላት ክምችት ነው ። በዓላት በሲኖዶስ ተቀንሰው ሰው የሥራን ክቡርነት በማወቅ በሥራ መስክ ተሠማርቶ ኤኮኖሚውን እንዲያዳብር ቢደረግ መልካም ነው ። ይህ ማሻሻያ በኦሪት ዘጸአት ም- ፳ ቁ- ፱ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመፈጸም ሌላያጐደለው ነገር የለም ። በአንፃሩም በኅብረተሰብአዊነት ፍልስፍና መሠረት ሠርተህ ራስህንና ወገንህን ዕርዳ የሚለውን መፍትሔ በተግባር ላይ እንዲውል አደረገ ማለት ነው ።

እንዲሁም ስለአጽዋማትም ሆነ ስለጸሎት በዘልማድ ከሚደረጉ ብዛትያላቸው አጽዋማትና ጸሎታት ይልቅ ፤ አነስ ያሉና እጠር ያሉ ሆነው ጥራት ያላቸው ቢሆኑ የተሻለ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ያለውን የጾምና የጸሎት አያያዝ መተንተን አያሻኝም ። እያንዳንዳችን በሚገባ እናውቀዋለንና ። ለማስታወስም ያህል ትንቢተ ኢሳይያስ ም- ፶፰ ቁ- ፫-፰ እና የማቴዎስ ወንጌል ም- ፮ ቁ- ፮ እንድታነቡ ከመጠቆም በስተቀር አስተያየቱን ለአንባብያን ትቼዋለሁ ።

ይህንንም ስል በሚገባ እንጹም ማለቴ ነው ። እያንዳንዱ ምእመንወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሔደው በአጭሩ ጸሎተ ማኅበርን ለመሳተፍ ፤ ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበልና ስብከተ ወንጌልን ለመስማት ነው ። ከጥቂቶቹ አድባራትና ገዳማት በስተቀር በአብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የሚገኙባቸው ጊዜያት ለምእመናን ምቹ የሚሆኑበት ሰዓቶች ተለይተው ሕዝቡ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ መልካም ይመስለኛል ቤተ ክርስቲያኑንና ሕዝቡን በተለይ ወጣቱን ትውልድ ሊያራርቁ ከሚችሉትም ሁኔታዎች አንዱ ይኸው የጊዜ ጉዳይ ይመስለኛል ።

ለምሳሌ በሰዓተ ሌሊት የሚካሔደው አገልግሎት ምስጋናና ጸሎት የሰው ልጅ ያለሥጋት ወደሚንቀሳቀስበት ወደሰዓተ መዓልት ቢለወጥ ፤ ወንድ ፤ ሴት ፤ ሕፃን ፤ ሽማግሌ ሳይባል የብዙ ምእመናን ተሳትፎ ይኖረዋል ብዬ እገምታለሁ ። ታዲያ ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች ሊያሻሽል የሚገባው ማን ነው ? ክርስቲያን ወይስ ቤተ ክርስቲያን ? በእውነቱ ክርስቲያኑን ወክለው በአስተዳደሩ ውስጥ ያሉት ሥዩማን ቤተ ክርስቲያን እነዚህንና ሌሎችንም ዓበይትጉዳዮች በቂ ጥናትን በመውሰድ እንዲያሻሽሉዋቸው ኃላፊነት ያለባቸው ይመስለኛል ።

ከአሁን ቀደም የነበረው መንግሥት እጁን ጣልቃ በማስገባት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሻሻል ዕንቅፋት ሆኖ መቆየቱ የሚታመን ቢሆንም ፤ ከለውጥ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ እንድትተዳደር ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በወጣው ዓዋጅ መሠረት ዕንቅፋቱ ተወግዷል። ጐልቶ የሚታይ የተሻሻለ ሥርዓት ግን እስከ አሁን ድረስ አልወጣም ። እንግዲህ የሚጠበቀው ምንድር ነው? ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጭቆና ብዛት የተነሣ በ፲፱፻፷፮ ዓ- ም- እንዳደረገው እንቅስቃሴና አብዮታዊ ለውጥ ሰፊው ምእመንም ተመሳሳይ የሆነ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ነውን ? ይህ መሆን የለበትም ። በቤተ ክርስቲያንም እንዲህ ያለው አድራጎት አይጠበቅም ። ይልቁንስ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ መንፈስ ነቅታና ተደራጅታ ሳትቀደም ቀድማ አስፈላጊውን የለውጥ ርምጃ እንድትወስድ አስተዳደሩ ቢበረታበት መልካምነው እላለሁ ።

ጸጋይ በርሄ

## ቤተ ክርስቲያናችን በለውጡ እንፃር ትራመድ

ቤተ ክርስቲያን ከለውጡ ጋር ወይንም ራሷ የምትመራበትንና የምትሻሻልበትን ፈለግ ማበጀት አለባት ። ይኸውም በለውጥ ነው ።

ለውጥ ስንል አንድ ነገር ካለመኖር ተነሥቶ ወደ መኖር የሚደርስበትን የለውጥ ዓይነት ሳይሆን ዕንቁላል ቀስበቀስ ወደ ጫጩት ፤ ከዚያም ወደዶሮ የሚደርስበትን ዓይነት ለውጥ ማለታችን ነው ።

ለመሻሻልና ፤ የተዛባውን ለማስተካከል ለውጥ ያስፈልጋል ። ለውጥ ያልዳሰሰው ነገር ቢኖር ጐጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም ። ሰዎች እንዲመሩበት ከተፈለገ ግን የተዛባውን ለማስተካከል የጥገና ለውጥ ሳይሆን ሥርነቀል ለውጥ የግድ ያስፈልጋል ።

ለምሳሌ የፍጥረታትን ታሪክ ብናስታውል በየወቅቱ የሚካሔድ ለውጥ አላቸው በዚሁ አንፃር ያለ ለውጥአዲስ ነገር መታየት አይችልም ። የጠፋውንም ለማረም የብዙኃኑን ፍላጎት ለማግኘት ለውጥ የሁሉም መስታዋት ነው ። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችን የሚያስፈልጋት ለውጥ ተፈላጊ ያልሆኑትን ሃይማኖት መሰል ልምዶችና ተፈላጊ ሆነው ለብዙዎች አመቺ ያልሆኑትን ሲሆን የለውጡ መካሔድ መጀመር የሚኖርበት ያው ከውስጡ ካሉ ኃላፊዎችና መሪዎች አገልጋዮችም ጭምር ነው ። የቤተ ክርስቲያናችን አመራርና ሂደት እንዲሠምርና እንዲያምር ቤተ ክርስቲያን ልትሰጥ የምትችለውን የሆነ ተቀባይነትና አመቺነት ያለውን ሁኔታ ለማስገኘት በሁሉም የታወቀ ዓይነት ለውጥ ያስፈልጋታል ።

እንደሚታየው ግን ይህቺ የሁሉም እናት የምንላት ቤተ ክርስቲያናችን ለተወሰኑ ሰዎች ማለትም በውስጡ ላሉት ብቻ የቆመች ትመስላለች፤ደግሞም ናት፤ከዚህም በላይ የመከፋፈሉና ያለመግባባቱ መንሥኤ አንዱ መነሻ ያለ ለውጥ የምታደርገው አካሔድ ሊሆን ይችላል ። ይኸም ለብዙዎች ባለማሰብ የሆነ ይመስላል ። እንደ ሕዝቡ ተቀባይነትና እንደጊዜውአካሔድ ብታደርግ ደግሞ የሁሉም ለመ





www.ethiopianorthodox.org

ሆንዕድል ይኖራታል ። ለዚሁምቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ ልታደርገው የሚገባውን ለውጥ ራሷ ብታካሒደው ለሌሎች ለውጥ አስገኝዎች ፤ ችግርን አይፈጥርም ። ወይንም ከመወቀስና ከመዝረክረክ ያድናታል ። እንዴት እናት ልጅዋን ከሕፃንነት ጀምራ ተንከባክባ አሳድጋ ራስ ካስቻለች በኋላ የሚቀጥለውን ደረጃ እንክብካቤ ማለትም በእርጅናቸው ጊዜ የሚያስ ፈልገውን ሁሉ ለማድረግና ጠባይን በማወቅ እንደየአመላቸው ለመሸነጋ ገል ለእናት ከልጅ ለልጅም ከእናት የቀረበ ሌላ አይገኝም ለቤተ ክርስቲ ያናችንም ለውጥለማስገኘት ከውስጡ ካሉት በቀር የሚያውቅላት የለም እናት ቤተ ክርስቲያናችንን ልጅ እን ደሌለው ለማያውቃት መተቻቻ ከመ ሆኗ በፊት ከሌላም ሁሉ እንድትድን ለውጡ ከውስጥ መፍለቅ አለበት ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የምታደርገው ለውጥ ለጥቅም እንጂ ለጉዳት አይሆ ንባትምና ።

ባሉበት ቆሞ መሄድ ለማንምሕያው ወይንም ተንቀሳቃሽ ፍጥረት የተሰጠ ባሕርይ አይደለም ። እባብ ሲያረጅ በተፈጥሮ የሚያደርገው የቆዳ ለውጥ እንደገና ለብዙ ጊዜ ያኖረዋል።ከዚያም በኋላ በአስፈላጊው ሁናቴ ሊለወጥ ይቻላል።ታዲያ የለውጥን አስፈላጊነት ከፍጥረቶች ጀምረን ብንመለከት እና ገኛለን ። ፍጥረት ሁሉ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ የሚያደርገው ብዙ ዓይነት ለውጥ አለ ። ከአለማወቅ ወደ ማወቅ መድረስ ትልቁ ዓይነት ለውጥ ሲሆን ወደ ማወቅ የደረስንበ ትን ዕውቀት ለውጡን በሥራ ለመተ ርጐም የሚደረግም ጥረት አለ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ወደኋላ እንድትቀርና በውስጡም ያሉት ብዙዎች የበይተመ ልካች እንዲሆኑ ወይም በድጐማ ለመ ኖር የሚፍጨረጨሩት ቤተ ክርስቲ ያን ስለምታደርገው ለውጥ የተነሣ ሊሆን ይችላል ። ታዲያ ቤተ ክርስቲ

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

አዲስ አበባ ፤

በኢትዮጵያ የሚገኙ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ተወካ ዮች የኢትዮጵያን ሕልውና ለመ ድፈር ለሚመጣ ጠላት ሁሉ » በሀ ገር ሃይማኖት አይለያየንም » የሚል መፈክር ይዘው ከመጋቢት ፲፱—፳፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ. ም. ድረስ የ፫ ቀን ሰሚናር አድርገዋል ። በሰሚናሩም መክፈቻ ዕለት በኢትዮጵያ የሚገኙ ትን ክርስቲያኖች በመወከል የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ንግግር ሲያደርጉ ፤ በእስልምና እምነት ተከታዮች ስም የታላቁ አንዋር መስጊድ ኢማም ንግ ግር አድርገዋል ። እንዲሁም ስለሀገ ሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የመንግሥት

ተከታዩ ወደ ፳፰ኛው ገጽ ዞሯል

ያናችን ያለ ለውጥ የምታደርገውርም ጃዋ ብዙዎችን የሚያሰቃይ ፤ ከዚህም የተነሣ የሚያርቅ ከሆነ የውጪዎችን እንዴት መሳብ ትችላለች ? ደግሞስ ከእናታቸው ኰብልለው ያሉትንበምን ማሻሻያ ትመልሳቸዋለች ? ለኰበለሉት ሲገርማት ፤ ያሉት እንዳይሸሹዋት ሁሉንም ልጆችዋን በዕቅፍ የምታደ ርግበትን ቀን ባታርቀው እጅግ መል ካምነው ።

በዚህ በዚህ ምክንያት ቤተ ክር ስቲያን ስትለወጥና አመቺ ሆና ስትራመድ ብዙ ዘመናት እየተቆጠሩ እንደዋዛ አልፈዋል ፤ ያለፈን ማንሣት ለፊተኛው መርሳት ምክንያት እንዳ ይሆነን እንጠንቀቅ ። የምታደርገው ለውጥ ቢኖር ባለሥልጣኖችን ማን ሣት ወይም ማቀያየር ብቻ ነው ። የዚህ ዓይነቱ ለውጥ በርሜል ቢለዋ ወጥ ጠጅን አያጣፍጥም እያሉአበው የሚናገሩትን እውነተኛ ተረትንይመ ስላል። ከዚያ በላይ ያለውን ለውጥ ግን ልታደርገው የሚገባት አይመስ ላትም ። ቤተ ክርስቲያናችንን የዚህ ዓይነት ስም ለበስ ለውጥ አይደለም ። የሚያስፈልጋት ። በተረፈ ግን ለውጥ እስካሁን እንኳን ከውስጧ ከገራረገራ ዋም አልደረሰም ብንል ስሕተት አይ ሆንም ። የቤተ ክርስቲያናችን በሥራ መዝረክረክ ፤ እርስ በርስ ያለመግባ ባት ፤ በተለያዩ መንገዶችም የዘር ፤ የጾታ ፤ የወገን የመሳሰሉትም ሁሉ ልዩነቶች መፈጠር ችግር የሚገጥማት ለውጥ የሚባለውን ነገር በሥራ ስለ ማትተረጉም ነው የውስጧ ችግሮች በሙሉ ሊቃለሉ የሚችሉት ለውጥን አምና በሥራ በምታሳይበት ጊዜ ነው።

የምትንቀሳቀስበትን መንገድ እራሷ በማዘጋጀትየለውጡ መሪና አስፈፃሚ ለመሆን ቀኖችን ባለመወሰን ሌትና ቀን በመንፈሳዊ ትጋትና እንቅስቃሴ የማያወላውልና መንፈሳዊ ድፍረት ጭምርን የተሞላ ቅን አስተሳሰብና ከመነሻው እስከ መድረሻውዕቅድ ወይም ዓላማ የተዋሐደ ው እንዲሆን ግድ ነው ።

ከዕንቅልፍ የምንነቃበት ሰዓት አልፏል እስኪ አሁን እንንቃ በሥራ ችንም የእግዚአብሔር ረድኤትና የጸጋ ስጦታም ጭምር እንዲበዛልን በጸሎት እየተጋን አሁን እንነሣ ።

አንተ የምትተኛ ንቃ ፤ ከሙታ ንም ተነሣ ፤ ክርስቶስም ያበራልሃል ።

ኤፌ ፩ ፣ ፲፪ (፭ ፣፲፬)

ንብረት አበበ



ከ፳፱ኛው ገጽ የዞረ

ባለሥልጣኖችም ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥተዋል ።

ሁሉም የልዩ ልዩ እምነት ተከ ታዮች ሰፋ ያለ የጋራ መግለጫ አውጥተዋል ።

✱ ✱ ✱

አቴን ፤ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ለእምነት ተከታዮች መንፈሳዊ ትምህርትመስጫ የሚሆን በመካከለኛ ሞገድ የሚሠራ ራዲዮ ጣቢያ ለማቋቋም ዕቅድ በማው ጣት ላይ ነው ተባለ ።

ለዚሁም ዕቅድ አወጣጥ የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ማኅ በር ተጠይቋል ።

የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ትምህር ቷን በመንግሥት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ አማካይነት በየሳምንቱ የግ ማሽ ሰዓት ፕሮግራም እንዳላት የዓ ለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር ጋዜጣ በ፳፯ኛው ቁጥሩ ገለጸ።

✱ ✱ ✱

ራባት ፤ በሞሮኮ የሚገኙት የወን ጌላዊት የሮማ ካቶሊካዊትና የግሪክ ፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስና የአንግሊካን አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ላይ በመሆን የሞሮኮ የአብያተ ክርስቲ ያናት የአንድነት ጉባኤ ጽ/ ቤት አቋ ቋሙ ሲል የዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት ማኅበር ( ዋን ወርልድ ) የተባ ለው መጽሔት ገለጠ ።

★ ★ ★

ሐባና በላቲን አሜሪካ የሚገኙት የወጣት መንፈሳዊ ማኅበር ስብሰባ ባለፈው ታኅሣሥ በኩባ ርእሰ ከተማ በሐባና ተደርጐ ነበር ። በዚህም ስብ ሰባ የኩባ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅ በር( ከባፕቲስት ፤ ከፕሬስፕቴርያን ፤ ከሜቶዲስት ከሮማ ካቶሊክ ፤ ከሰል ቬሽን አርሚ ፤ ከአድቬንቲስት ከወን ጌላዊት ቤተ ክርስቲያን እና በሀገሪቱ ካሉት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ) የተውጣጡ ወጣቶች አብያተ ክርስቲ ያናትን በመወከል በስብሰባው ተካፍ ለዋል ።

የስብሰባውም ዓላማ በኅብረተሰባዊ ፍልስፍና በሚመሩ አገሮች የሚገኙ ክርስቲያን ወጣቶች ማኅበራት ሀገራ ቸውን ከረሃብ ፤ ከድንቁርና ፤ ከበሽ ታና ከሀገር ፤ ወረራ ጠላት ለመከላከል መሥዋዕት በመሆን ማገልገል ግዴ ታቸው መሆኑና የአለንበትንምዓለም ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ የሚደርስበትን መንገድ ለመቀየስ ነበር ።

ስብሰባው በሜቶዲስት ሆስቴልና ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ፤ ለውይይት የቀረቡትም አርእስቶች« ወጣቶችና ኅብረተሰቡ » ወጣቶችና ቤተ ክርስ ቲያን » ፤ ወጣቶችና ኢኩሜኒዝም ወይም ወጣቶችና የክርስቲያናዊዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚሉ እንደነበሩ ቁጥሩ ፬/፵፫ የሆነው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መጽሔት ገልጧል ።

★ ★ ★

የጀርመን ክርስቲያን ወጣቶችን አቋም የሚያስረዳ መመሪያ ወጣ ፤

የወጣቶችን መንፈሳዊ አቋም የሚ ያስረዳ መመሪያ ታትሞ እንዲሰራጭ ያደረገው በምዕራብ ጀርመን የሚገ ኘው የፕሮቴስታንት ማዕከላዊ ጽ/ ቤት ሲሆን ፤ ጽሑፉን ያዘጋጁት ቀሲስ ሄልሙትሂይሸለን የዚሁ ማዕ ከል ጽ/ ቤት ዲሬክተር ናቸው ።

ይህ መመሪያ ወጣቶች በመንፈሳዊ ረገድ ሊከተሉት የሚገባውን ሚና የሚያስገነዝብ ሲሆን ፤ መሠረተ አሳቡ በልዩ ልዩ የክርስትና ክልል እምነት ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ሁሉ እንዲያጠቃልል ሆኖ የቀረበ ነው ። ከዚህም በስተቀር ይህ መመ ሪያ የያዛቸው ፍሬ ነገሮች መንፈ ሳዊ አቋማቸው ለተናጋባቸው ወጣቶች እርካታን እንዲሰጣቸው ማለትምወደ ተፈላጊው ግብ እንዲመራቸው ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ፤ ጠቃሚ የሆነ መግ ቢያም የሰጡት የጀርመን ፕሮቴስ ታንት አንድነት ድርጅት ጳጳስ ሄል ሙት ናቸው ሲል ቁጥሩ ፲፫/ ፸፰ የሆነ የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን መንፈሳዊ መጽሔት ገልጧል ።

✱ ✱ ✱

ስታምቡል የሉተራውያን እምነት ተከታይ መሪዎች በቱርክ ሀገር የሚ ገኘው የዓለም አቀፍ የሆነውን ፓት ርያርክ ጐበኙ ።

መልእክተኞቹ የወዳጅነት ጉብ ኝት ለማድረግ ኢስታንቡል እንደገቡ በዓለም ላይ የሚገኙ የ፪፻ ሚሊዮን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሪና የቁስጥንጥያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅ ዱስ ቀዳማዊ ድሜጥሮስ ተቀበሉዋ ቸው ።

ስለዚሁ ጉብኝት የተጻፈው ዜና እን ደሚያመለክተው ባለፉት አምስት መቶ ዘመናት ተቀራርበው ስለአብ ያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ወይም ኤኩሙኒዝም ያልተወያዩት ሁለቱ የእ ምነት ክፍሎች በወዳጅነት ስለአብ ያተ ክርስቲያናት ግንኙነት እንደሚ ነጋገሩ ታውቋል ።

መንበረ ፓትረካናው ቁስጥንጥንያ የሆነው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመናት የቆዩ አብያተ ክርስቲ ያናት በአንጾኪያ በእስክንድርያ፣ በኢ የሩሳሌም ፤ በግሪክ ፣ በሳርቢያ ፣ በሞ ስኮ ፣ በፊንላድና በሩማኒያ እንዳሉት መሆኑን ቁጥር ፲፫/ ፸፰ የዓለም የሉ ተራውያን ፌዴሬሽን መንፈሳዊመጽ ሔት ገልጧል ።

✱ ✱ ✱

ቤይሩት ፤ የአርመን ክርስቲያን ተማሪዎች ስብሰባ በሊባኖስ ፤

ብዛታቸው አራት መቶ የሚሆን የአርመን ተማሪዎችና ሠላሳ የሚደ ርሱ ፕሮፌሰሮች የተገኙበት ፤ እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ዚሁም ፕሮቴስታንቶች ፤ የካቶሊክና የኦርቶዶክስ ተከታዮች ተካፋይ የሆኑበት ስብሰባ ለመጀመሪያ ጊዜ በቤይሩት አጠገብ በምትገኝ አንቴሊያስ በተባለች ሥፍራ ተካሒዷል ። ይህ በብፁዕ ወቅዱስ ካቶሊክስ ዳግማዊ ካሪኪን የሲሊሲያ መሪ ተጠባባቂነት የተካሔደው ጉባኤ ወጣቶቹ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ስለ ማኅበራዊ ኑሮ በሰፊው እንዲወያዩ አስችሏቸዋል ።

በዚህ ስብሰባ ላይ በልዩ ልዩ አርእስቶች የቀረቡት ንግግሮች ያተኮሩት « የወጣቱ ሚና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ » በሚለው ላይ ነው ። በተለይም ሚስተር ገብርኤል ሐቢብ የማዕከላዊው ምሥራቅ የአብያተክርስቲያናት አንድነት ዋና ጸሐፊ ባደረጉት ማብራሪያ ፤ ምናልባት ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን እነርሱ በፈለጉዋት ዓይነት ሁና አላገኙዋት ይሆናል ፤ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ያላትን ሕልውና እንድትጠብቅ ፤ መሪዎቿም ተሐድሶ እንዲያገኙ ክርስቲያኖች እንዲተባበሩና የቤተ ክርስቲያንንም አገልግሎት ለሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ ኃላፊነታቸው ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ካቶሊኮስ ዳግማዊ ከራኪን በበኩላቸው ለወጣቶቹ በሰጡት ቃል ፤ ቤተ ክርስቲያን ላረጁ፤ ላፈጁና ለሙታን ብቻ የተሰጠች አድርገው መገመትን እንዲተዉ መክረዋቸዋል ። ብፁዕነታቸው ቀጥለው ሲገልጹ ወጣቶች ስለቤተ ክርስቲያናቸው ፤ ማወቅ ፤ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ የሚሰጡትን አገልግሎት ተከታትለው ማጥናትና መገንዘብ ተግባራቸው መሆኑን አጠንክረው አስገንዝበዋል ሲል ቁጥሩ ፳/፺፭ የሆነው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መጽሔት ገልጧል ።

<u>ስዊዘርላንድ ፤</u> ኢኮሙኒዝም በወጣት ኦርቶዶክስ ዕድገት ውስጥ ፤

በቅርቡ ባለፈው ዓመት በስዊትዘርላንድ ከተማ በባስል ላይ ከሐያ ሁለት የኦርቶዶክስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ተቋም የተውጣጡ ምሁራንየሚገኙበት ጥንታዊ ስብሰባ የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ዓለም የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበር እንደሚከፍት ተገለጠ ። በዚህና በሌሎችም ተመሳሳይ ጉባኤዎች ላይ በተለይም ኦርቶዶክስ የሆኑ ወጣቶች ሊሠለጥኑ የሚችሉባቸው ዘዴዎች ጥናት ይደረግባቸዋል ። ከዚህም በስተቀር ይህ በባስል የሚካሔደው ስብሰባ ስለከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ማለትም ስለቤተ ክርስቲያን እምነታዊ ሥነ ሥርዓት ጥናት ይደረጋል ። እንደዚሁም የመንፈሳዊ ትምህርት ለአማኒያን በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ በሚደርስበት ዘዴ ውይይት ይካሔዳል። ቀጥሎም የኦርቶዶክስን የመንፈሳዊ ትምህርት ከኤኮሙኒዝም አንፃር ይታያል ።

በሌላ በኩል የዓለም ሃይማኖተ አበው ማኅበር (የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን) ሁለተኛውን የወጣት ኦርቶዶክስ ተማሪዎች ስብሰባ ከመስከረም ፲፪—፲፰—፲፱፻፸፩ ዓ- ም- በካይሮ እንደሚያደርግ ታውቋል ። በዚህ ስብሰባ ላይ ስድሳ ተካፋዮች ተገኝተው «ክርስቲያናዊ ታዛዥነትና ለአርነት ምርምር ዛሬ በሚል ርእስ ላይ ይነጋገራሉ ።

ይህ የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን ቀደም ሲል ስብሰባውን በመስከረም ወር ፲፱፻፷ ዓ- ም- ኒኮሲያ ላይ አድርጎ ነበር ። ይህ ፌዴሬሽን የኦርቶዶክስ ተማሪዎችና መን

# የእግዚአብሔር ህላዌ

ከቄስ መክብብ አጥናው

« - - - አንድ ሰው ልብ ያለው መሆኑን ላያውቅ ይችላል ። ነገር ግን ያለ ልብ ሊኖር አይችልም ። እንደዚሁም አንድ ሰው ስለራሱ ሃይማኖት እንደ ሌለው (ማለትም የእግዚአብሔርን ? መኖር እንደማያውቅ አድርጎ ያስብ ይሆናል ። ይሁን እንጂ ለጊዜው የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ቢኖረውም ያለሃይማኖት መኖር ከቶ አይችልም። » ታላቁ የሩሲያ ደራሲ ቶልስቶይ)

« - - - የሳይንስ ጥናትና ምርምር እንኳ ራሱ አንድ ቀን ፍጥረትን ከበላይ ሆኖ ከሚመራና ከሚያስተዳድር ከአንድ ኃያል ፈጣሪ ዘንድ እንደሚያ

ተከታዩ ወደ ፳፯ኛው ገጽ ዞሯል

ፈሳዊ ምሁራን በኤኩሚኒካል ረገድ አስተዋጽኦ እንዲሰጥ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ። ይህ የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን በዘጠና ስድስት አገሮች አባላት ያሉት ሲሆን ይህም አሥራ አምስት የሚደርሱ የኦርቶዶክስ ማኅበራትን ያጠቃልላል ሲል ቁጥሩ ፳+፵፭ የሆነው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መጽሔት ገልጧል ።

★ ★ ★

<u>ስቶክሆልም ፤</u>—የስዊድን ቤተክርስቲያን ተከታዮቿን የሁዳዴን (ዓቢይ ጾም) ምክንያት በማድረግ የምግባቸውን ወጪ በመቆጠብ በዓለም ለሚገኙ ለልማትና ለርዳታ መቋቋሚያ የሚሆን ገንዘብ እንዲያዋጡ ባስተለፈችው መልእክት መሠረት ከስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስድሳ ሺህ የኢትዮጵያ ብር በላይ በሦስቱ ተከታታይ ዓመታት መዋጣቱን ቁጥሩ ፲፭/፸፰ የሆነው የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ጋዜጣ አስታወቀ



# የእግዚአብሔር ህላዌ

ከ፳፮ኛው ገጽ የዞረ

ቀርበን ሊታመን ይቻላል ። ዓለሙን የሚገዛና የሚመራው አንድ ከፍተኛ ኃይል በእርግጥ አለ ። » (ማክስ ፕላንክ ጀርመናዊ ሊቅ)

«ኅልፈትና ወሰን የሌለው ፤ ሁሉን አዋቂና ኃያል የሆነ ፈጣሪ ባጠገቤ ሲያልፍ አየሁት ። በእርግጥ በአካል ፊት ለፊት አየሁት ማለቴ አይደለም። ያየሁት አስደናቂ በሆነው በፍጥረት ሥራው በኩል ነው ። » በዚሁ በፍጥረት ሥራውም በኩል እንዳየሁትወዲያውኑ በመደነቅ እንደደንቆሮና ዲዳ ዓይነት ሆንሁ ። በእውነቱ ከትንሹ እስከ ትልቁ ድረስ ያው ሥራው ሁሉ የቱን ያህል ጥበብና ኃይል ይታይበት ይመስላችኋል ? እንዴትስ ዓይነት ፍጹም ድንቅ ነው ? » (ሊኔ የተባለ ሊቅ የተናገረው )


« - - - ፈጣሪዬ ሆይ ! ሥራህን እንዳመሰግን ስለፈቀድህልኝ እባርክኸሁ በሰጠኸኝ አእምሮ የሕይወቴን መልእክት ከፍጻሜ አደረስሁ ። የሥራህንም ተአምር ለሰዎች ገለጥሁ ። ነገር ግን ምናልባት ባደረግሁአቸው ሥራዎች አንተ የምትከብርበትንመንገድ ከማሰብ ይልቅ ለራሴ ስምና ዝና ብዬ በውዳሴ ከንቱ ያደረግሁት ነገር ቢኖር በደግነትህና በቸርነትህ ይቅር በለኝ ። ሕግንና ሥርዓትን የተሞላችሁ የሰማይ ዓለማት ሁሉ ጌታን አመስግኑት ፤ ነፍሴም ይህን ጌታ አመስግኝ ። » (ኬፕለር ጀርመናዊ ሊቅ)

«የሰው አእምሮ በተፈጥሮው የራሱንና የመላውን ዓለም ጌታ (ፈጣሪ) ለማግኘትና ለመርዳት የሚባዝን ነው (ጂ' ቼዋሊዬር የተባለ ሊቅ)

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሊቃውንትና የታላላቅ ሳይንቲስቶች አነጋገር እንደሚያመለክተን ፤ ይህንዓለም አከናውኖ የፈጠረ ፤ ባጠቃላይ የፍጥረትን ሕግጋት የሠራና የወሰነ አንድ ኃያል አምላክ መኖሩን ይጠቁማል ።ታዲያ ዝሆን ይኸውልህ ቢሉት ዱካው የታል ? ብሎ በዓይኑ የሚያየውን ወይም ከፊቱ የቆመውንና በእጅ ሊዳሰስ የሚችለውን እንስሳ መኖሩን ለመካድ ሞከረ እንዲሉ ፤ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የእግዚአብሔርን ህላዌለማ ካካድ ቢሞክር ደካማ ፍጡር መሆኑን እንጂ አዋቂነቱን አያመለክትም ።

ደግሞም ልናውቀው የሚገባ በእግዚአብሔር ህላዌ ማመንና እርሱን ማምለክ ከሥልጣኔ እድገት የሚገታ አይደለም ። መካድም ደግሞ ፍጹም ተራማጅነትን አያሳይም ። ፍጹም አማንያን ሆነው የለየላቸው አድኃሪዎች የሚሆኑ ሊኖሩ ይችላሉ ። ደግሞ ፍጹም አማኞች ሆነው ተራማጆችም ሊሆኑ እንደሚችሉ ከየትኛውም ሥርዓተ ኑሮ መማር ይቻላል ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚል «እኛ የእግዚአብሔርን ህላዌ ብንክድ ለርሱ ክብር የሚጎድልበት አይደለም ። እርሱ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም ። የፍጥረት ሥሪው ሁሉ የርሱን ህላዌና ድንቅ ሥራውን ይመሰክራል ። »

ስለዚህ ስለእግዚአብሔር ህላዌ የቀድሞ አበው ሊቃውንትና ሳይንቲስቶች ብቻ ሳይሆኑ ፤ ከአሁኑምዘመን ታላላቅ የጥበብ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ በሚገባ እምነውበት የተቀበሉት መሆኑን አምነን ሌሎችንም ማሳመን ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑንመገንዘብ ይገባል ። (ይቀጥላል)



## ምእመናን ሆይ !

በክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ሀብቶቿ ምእመናን ናቸው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እያፈሰሰ ጉዳት አስከትሏል፤የሥላሴ ፍቅር የጠራችሁ፤ ለቤተ እግዚአብሔር መጠገኛ እጃችሁን እንድትዘረጉ ተጋብዛችኋል ።

[illegible] ኮሚቴ



www.ethiopianorthodox.org

# የኢ.ት | መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዓምድ

## የኢየሱስ ከሞት መንሳት ።

፩ ፣ እሑድ ጠዋት በማለዳ ገና ጎሕ ሳይቀድ መግደላዊት ማርያም ወደኢየሱስ መቃብር ሔደች ። እዚያም እንደደረሰች መቃብሩ ተዘግቶበት የነበረው ድንጋይ ከመቃብሩ በር ላይ ተነሥቶ አየች ። ፪ ፣ ስለዚህ እስዋ ወደስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደውወደ ነበረው ወደሌላው ደቀ መዝሙር እየሮጠች ሔደችና «ጌታን ከመቃብሩ አውጥተው ወስደውታል ። የት እንዳኖሩትም አላውቅም» አለቻቸው። ፫ ፣ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወጡና ወደመቃብሩ ሔዱ። ፬ ፣ ሁለቱም አብረው ይሮጡ ነበር ።ነገር ግን ሌላው ፈጥኖ ሮጠና አስቀድሞ ወደመቃብሩ ደረሰ ። ፭ ፣ ጎንበስ ብሎ ወደመቃብሩ ሲመለከት የከፈኑ ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ ። ነገር ግን ወደ ውስጥ አልገባም ። ፮ ፣ ስምዖን ጴጥሮስም ያየውን ደቀ መዝሙር ተከትሎ መጣና ወደመቃብሩ ውስጥ ገባ ። እሱም የከፈኑ ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ ። ፯ ፣ የኢየሱስ ራስ የተጠቀለለበትንም ጨርቅ ከከፈኑ ጨርቅ ጋርሳይሆን ለብቻው በሌላ ሥፍራ ተጠቅልሎ እንደተቀመጠ አየ ። ፰ ፣ ቀጥሎም ያ አስቀድሞ ወደመቃብሩ የደረሰው ደቀ መዝሙር ወደመቃብሩ ውስጥ ገብቶ አየና አመነ ። ፱ ፣ ምክንያቱም «ኢየሱስ ከሞት መነሣት ይገባዋል» የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ገና አልተገነዘቡም ነበርና ነው ። ፲ ፣ ከዚህ በኋላ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ተመልሰው ወደቤታቸው ሔዱ ።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደታያቸው

፲፱ ፣ በዚያኑ ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን በመፍራት በራፎቻቸውን ዘግተው በቤት ውስጥተሰብስበው ነበር ። በሮቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወደተሰበሰቡበት ቤት ገባ ። በመካከላቸውም ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን ! » አላቸው ። ፳ ፣ ይህንንም ብሎ እጆቹንና ጎኑን አሳያቸው ። ደቀ መዛሙርቱ ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው ። ፳፩ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንደገና «ሰላም ለእናንተ ይሁን ! አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ» አላቸው ። ፳፪ ፣ ይህንንም ብሎ «እፍ» አለባቸውና « መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ። ፳፫ ፣ እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ይቅር አይባልላቸውም» አላቸው

እነዚህ ንባቦች የተቀዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ይህን ካነበቡ በኋላ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝተው እንዲያነቡ እናሳስባለን ።


### ማሳሰቢያ

1ኛ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት "ድምፀ ተዋሕዶ" የተሰኘ ጋዜጣ ከአሁን በፊት ለ14 ዓመታት ያህል እያሳተመ ለምእመናን እንዲዳረስ ሲያደርግ ቆይቷል ።

አሁን ግን በይበልጥ ከመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ጀምሮ በማኅበርተኝነትም ሆነ በበዓላት ቀን ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚዳረስበትን መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆነ ይህንን ማሳሰቢያ የሚያነቡ ሁሉ አስተያየታቸውና ትብብራቸው እንዳይለየው ያሳስባል ።

2ኛ/ መንፈሳውያን መልእክቶችን መንፈሳውያን የሆኑ ዘመናውያን መዝሙሮችንና ጥንታውያን ዜማዎችን በካሴት እየቀረፀ ካሴት ለማያቀርቡ የካሴት ዋጋ $5 የአገልግሎት ደግሞ 2 ብር ብቻ እያስከፈለ የሚሰጥ መሆኑን በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ማሳሰባችን ይታወሳል ።

አሁንም በዚሁ ሁኔታ የቀጠለ መሆኑን እንገልጣለን ።



አድራሻችን አራት ኪሎ ብሔራዊ ሽንጐ ፊት ለፊት
የስልክ ቁጥር 11 - 66 - 16
የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ



የሙካሽ ሥራ

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ካቴድራል ጽ ቤት ከሚያካሂዳቸው የሥራ ዘርፎች

በእነዚህም ሆነ ወደፊት በምናስተዋውቃችሁ ዝግጅቶች ለመጠቀም የምትሹ ለማንኛውም ብትችሉ ወደካቴድራሉ ሱቆች ሄዳችሁ ለመረዳት ሞክሩ ።

ባትችሉ በስልክ ቁጥር 120170
በፖ. ሣ. ቁ. 3137 አዲስ አበባ ብላችሁ ጠይቁ



የሥጋጃ ሥራ



www.ethiopianorthodox.org